አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


# የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች፤ በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ


ይታያል ወርቁ



መጋቢት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች፤ በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ


ይታያል ወርቁ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


ለተግባራዊ

ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.

ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


መጋቢት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

# የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

# ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

## የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች፤ በ8ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ

ይታያል ወርቁ

የፈተና ቦርድ አባላት

[illegible] _____

አማካሪ ቀን ፊርማ

[illegible] 29/07/03 _____

ፈታኝ ቀን ፊርማ

መጋቢት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ሳይሰለቹ ጠቃሚ አስተያየቶችን በመለገስ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ዶክተር አረጋ ኃ/ሚካኤል ያለኝ ውስጣዊ አክብሮት፣ አድናቆትና ምስጋና የላቀ ነው፡፡

በሁለተኛ ድግሪ መርሃ ግብር ኮርስ ከሰጡኝ ሁሉም መምህራን የቀሰምኩት ዕውቀት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥናት ያበረከተው አስተዋጽኦ የሚናቅ አይደለም፡፡ ለዚህም መምህሮቼን ማመስገን ወደድኩ፤ ከልብም አመሰግንኳቸው ፡፡

ጥናቱን በማከናውንበት ጊዜ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለተባበሩኝ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች፣ መምህራንና ተማሪዎች፣ ኮምፒውተር በመስጠት ላገዙኝ ለተግባሩ መንገሻ፣ ለጥላሁን ከበደ፣ እንዲሁም በተፈለገው ጊዜና ሰዓት በመገኘት ሳትሰለች በመጻፍ ለተባበረችኝ ለወ/ሪት አርማዬን አደራ ያለኝ አክብሮትና ምስጋና የተለየ ነው፡፡

በመጨረሻም በሐሳብም ሆነ በገንዘብ ለረዱኝ ጓደኞቼ፣ ለሬድዋን በሪሁን፣ ለእዮብ ነጋ፣ ለውብሸት አሕመድ፣ ለፈንጅ ታደል፣ ለማሙሽ እጀታ፣ ለሐብታሙ ፈቀደና ለውድ ባለቤቴ አበባ ቢራቱ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርብኩ፡፡

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1 ስለ ምንባቦች አቀራረብ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ....................38

ሠንጠረዥ 2 መምህራን በንዑሳን የምንባብ አተገባበር ትምህርት ላይ ያላቸው ግንዛቤ............................................................................39

ሠንጠረዥ 3 አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ሂደት የመምህራኑ ሚና.............40

ሠንጠረዥ 4 የቅድመ ንባብ ትምህርት ትግበራ.........................................42

ሠንጠረዥ 5 የቅድመ ንባብ ትምህርት ተግባራት ......................................42

ሠንጠረዥ 6 የምንባቦች ትምህርት ......................................................44

ሠንጠረዥ 7 የምንባብ ትምህርት አቀራረብ ሂደት .................................46

ሠንጠረዥ 8 የድህረ ንባብ ትምህርት ትግበራ ........................................47

ሠንጠረዥ 9 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ትኩረት ከአይነት አንጻር ...............50

ሠንጠረዥ 10 የአንብቦ መረዳት ስልቶች ትምህርት.....................................52

ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና ..........I

የሠንጠረዥ ማውጫ ..........II

አጠቃሎ ..........III

ሙዳየ ቃላት..........IV

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ..........1

1.2 አነሳሽ ችግር..........3

1.3 የጥናቱ ዓላማ ..........3

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ..........4

1.5 ጥናቱ ገድብ ..........4

1.6 ያጋጠሙ ችግሮች..........5

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳን

2.1 የምንባብ ምንነት..........6

2.2 አንብቦ መረዳት ምንድንነው? ..........7

2.3 የንባብ ትምህርት ዓላማዎች ..........10

2.4 የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ..........11

2.4.1 የቅድመ ንባብ ትምህርት ..........11

2.4.2 የንባብ ጊዜ ትምህርት..........14

2.4.3 የድኅረ ንባብ ትምህርት..........15

2.5 የንባብ ትምህርትን በመተግበር ረገድ የቋንቋ መምህራን ሚና ..........17

2.6 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች..........19

2.6.1 ቀጥተኛ ጥያቄዎች ........ 20
2.6.2 የትንበያ ጥያቄዎች ........ 20
2.6.3 የግምገማ ጥያቄዎች ........ 20
2.6.4 አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎች ........ 21
2.7. የውጤታማ አንባቢ ባህሪያት ........ 21
2.7.1. በዓላማ ማንበብ ........ 21
2.7.2 የመገመት ችሎታ ........ 22
2.7.3 ቀደምት ዕውቀትን ለግንዛቤ መጠቀም ........ 22
2.7.4. የቃላትን ፍቺ ከዐውድ መረዳት ........ 22
2.7.5 ለግል ንባብ ትኩረት መስጠት ........ 23
2.7.6 ንባብን ከተገቢ የማንበብ ስልትና ፍጥነት ጋር ማስማማት ........ 23
2.8 የንባብ ስልቶች ........ 24
2.8.1 ትንበያ ........ 24
2.8.2 ማስታወሻ መውሰድ ........ 25
2.8.3 ድጋሚ ንባብ ........ 25
2.8.4 ማጠቃለያ ........ 25
2.8.5 ቅኝት ........ 26
2.9 የንባብ ክሂሎች ........ 26
2.9.1 የትኩረት ንባብ ........ 26
2.9.2 የአሰሳ ንባብ ........ 27
2.9.3 የእይታ ንባብ ........ 27
2.9.4 አውዳዊ ንባብ ........ 27
2.9.5 ሠፊ ንባብ ........ 28
2.9.6 ሂሳዊ ንባብ ........ 28
2.10. የቀደምት ሥራዎች ቅኝት ........ 29

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴ

3.1 የጥናቱ ዘዴ ........ 31
3.2 የመረጃ ምንጮች ........ 31

3.3 የናሙና አመራረጥ ........................................................................ 31

3.4 የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ........................................................................32

3.4.1 ምልከታ ........................................................................ 32

3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ ........................................................................ 33

3. 4.3 የቡድን ቃለ መጠይቅ ........................................................................ 34

3.5 የጥናቱ ክንውን ........................................................................35

3.6 የመረጃዎች አተናተን ዘዴ ........................................................................35

ምዕራፍ አራት

የመረጃዎች ትንተና

4.1.የተጠኚ መምህራን ዳራ ........................................................................ 37

4.2. ንባብን በማስተማር ሂደት የመምህራን ሚና ........................................................................ 39

4.3. የአንብቦ መረዳት ትምህርት ደረጃዎች ........................................................................ 41

4.3.1 የቅድመ ንባብ ትምህርት ........................................................................ 41

4.3.2 የንባብ ጊዜ ትምህርት ........................................................................ 43

4.3.3 የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ........................................................................ 45

4.3.4 የድህረ ንባብ ትምህርት ........................................................................ 46

4.4. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ........................................................................ 48

4.4.1. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ባሕርይ ........................................................................ 48

4.4.2 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ትኩረት ከአይነት አንፃር ........................................................................ 48

4.4.3 የአንብቦ መረዳት ስልቶች(Strategies) ትምህርት ........................................................................ 51

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

5.1 ማጠቃለያ ........................................................................ 54

5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች ........................................................................ 55

ዋቢ ጽሑፎች........................................................................ 58

አባሪ አንድ ........................................................................61

አባሪ ሁለት ........................................................................65

አባሪ ሦስት ........................................................................71

አባሪ አራት........................................................................72

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በቡለን ወረዳ ስምንተኛ ክፍልን በሚያስተምሩ ሶስት 1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብን በመፈተሽ ላይ የተመሰረተ ነው። ጥናቱን ለማካሄድም ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፣ እነሱም ምልከታ የጽሑፍ መጠይቅና የቡድን ቃለመጠይቅ ናቸው። በእነዚህም መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች በዋናነት ገላጭ የምርምር ዘዴን መሰረት በማድረግ የተተነተኑ ሲሆን፤ ውጤቱም በትምህርት ቤቶቹ ይሰጥ የነበረው የአንብቦ መረዳት ትምህርት በጥንታዊ አቀራረብ ዘዴ ላይ የተመሰረተ እንደነበር አመልክቷል። ከዚህም በመነሳት መምህራንን በማሰልጠን ላይ የሚገኙ ተቋማት ለንባብ ትምህርት የተለየ ትኩረት ቢሰጡ፤ መምህራኑ ስለ ንባብ ትምህርት በተለያዩ ምሁራን የተዘጋጁ ጽሑፎችን በማንበብና ከሙያ አጋሮቻቸው ጋር በመወያየት ግንዛቤያቸውን ለማጎልበት ቢጥሩ፣ የንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ አጫጭር ስልጠናዎችን በማዘጋጀት መመህራኑ እንዲሳተፉ ቢደረግ የተሻለ የንባብ ትምህርት ለመስጠት ያግዛቸዋል የሚሉ ዋና ዋና የመፍትሔ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል።

## ሙዳየ ቃላት

| | |
|---|---|
| -ሃሳብ ማመንጨት | Brain Storming |
| -የቃል ንባብ | Oral- reading |
| -የመገመት ክሂል | Predictive Skill |
| -ሚና ክንውን | Role playing |
| -ቀደምት እውቀት | Prior Knowledge |
| -ተነሳስኦት | Motivation |
| -ኑባሪያዊ | Authentic |
| -ቢጋር | Outline |
| -አንብቦ መረዳት | Reading Comprehension |
| -የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች | Pre-reading questions |
| -የንባብ ስልቶች | Reading strategies |
| -የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች | While reading questions |
| -የድህረ ንባብ ጥያቄዎች | Post-reading question |

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት ዓላማ-መራሽ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይኸውም በዋናነት አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማስተማር ነው፡፡ እነዚህም የማፍለቅና የመቀበል ክሂሎች ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ የማፍለቅ ክሂሎች መናገርና መፃፍ ሲሆኑ የመቀበል ክሂሎች ደግሞ ማዳመጥና ማንበብ ናቸው፡፡ ከመቀበል ክሂል አንዱ የሆነው የንባብ ክሂል ትምህርት ዋና ዓላማ ደግሞ ተማሪዎቹ ከተለያዩ የአነባብ ስልቶች ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግና የቀረበውን ጽሁፍ አንብበው እንዲረዱ ማስቻል ነው (Silberstein, 1994፣12) ፡፡

Willams (1984፣2)፣ "ንባብ በተፃፉ ነገሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ሐሳብ የመረዳት ሂደት ነው" በማለት ይገልፃሉ፡፡ እኚሁ ምሁር ይህን ሐሳብ ሲያብራሩ፣ በዚህ ብያኔ መሠረት "መረዳት" የሚለው መሠረታዊ ቃል ነው፡፡ ምክንያቱም የሚያነቡትን ካልተረዱ ንባብ ሊባል አይችልምና" በማለት ይጠቁማሉ፡፡ Goodman (1970፣260) ይህን ሐሳብ ሲያጠናክሩት ንባብ ከቀረበው ጽሑፍ ውስጥ አንባቢው የሚፈልገውን ነገር ብቻ እየመረጠ ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበት ሂደት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ሐሳብ ጋር በተያያዘ Nunan (1991-33) የተፃፉ የቋንቋ ምልክቶችን ማለትም ፊደላትን፣ ቃላትን፣ ሐረጋትን እና ዓረፍተ ነገሮችን በመተርጎም መልዕክት የመረዳት ሂደት ነው በማለት ሲያስረዱ፣ Grellet (1981፣3) ደግሞ አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ጽሑፍ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ በማውጣት የጽሑፍን መልእክት የመረዳት ችሎታ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

የሰው ልጅ መረጃ ከሚያገኝባቸው መንገዶች አንዱ በማንበብ ነው፡፡ በመሆኑም ከትንሿ በራሪ ጽሑፍ ጀምሮ እስከ ረጅም ልቦለድ ድረስ ለተለያየ ዓላማ የማንበብ ልምድ ሊያዳብር ይችላል፡፡ በሰሌዳ ላይ በሚለጠፉ ማስታወቂያዎች፣ በዕለት ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ በማስተማርያና መማሪያ መጻሕፍት ከድኅረ ገጽና ከመሳሰሉት ላይ መረጃ የማሰባሰብ ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል (Grellet 1981፣ 3-4)፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱን

ነገር ማንበብ ጊዜን፣ ገንዘብና ጉልበትን በከንቱ ማባከን ያስከትላል። ስለዚህ የተገኘውን ነገር ሁሉ ማግበስበስ የንባብ ፍላጎትን ከመቀነሱም ባሻገር የንባብ ልምድ እንዳይዳብር ስለሚያደርግ መርጦ ማንበብ ተገቢ እንደሆነ Grellet (1981፣ 3)፣Harmer (1990፣ 18) ያስረዳሉ። የንባብ ትምህርት ቀዳሚ ተግባር ተማሪዎቹ ለንባብ ማስተማሪያነት የተመረጠውን ጽሑፍ እንዲያነቡ ማድረግ ሊሆን ያሻል። የመምህራኑ ሚናም ለምን ዓላማ፣ ምንና እንዴት ማንበብን የተገነዘቡና በራሳቸው ጥረት ችግራቸውን ለመቅረፍ የሚችሉ ተማሪዎችን ማፍራት በመሆኑ ረብ-የለሽ ከሆነ ጣልቃ ገብነት ታቅበው አብዛኛውን ሰዓት ለተማሪዎቹ ማዋል ይጠበቅባቸዋል (Silberstein፣1994፣10)። ስለሆነም ተማሪዎቹ መምህሩ የሚያነበውን ጽሑፍ እንዲያዳምጡ፣ ጥያቄዎች እንዲጽፉና መልስ እንዲፉልጉ፣ ወዘተ. ከማድረግ በመቆጠብ አብዛኛውን የትምህርት ሰዓት ተማሪዎቹ ራሳቸው እንዲያነቡ ማበራታት ያሻል። ይህ ካልሆነ ዋናው ግብ ተዘንግቶ ለተንዳኝ ጉዳዩች ትኩረት እንደተሰጠ ይቆጠራል።

ባጠቃላይ የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ተገቢውን ስልት የተከተለ መሆኑ ለክሂሉ መዳበር ታላቅ አስተዋጽኦ አለው። ምክንያቱም ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ለማንበብ የሚነሳሱት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ማራኪና ሳቢ ሲሆን ነው። ስለዚህ መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚጠቀምባቸው የንባብ ማስተማሪያ ዘዴዎች ዘፈቀዳዊ መሆን የለባቸውም። አሰልቺነት ባሕሪይ የሚታይባቸውን ዘውትራዊና ተደጋጋሚ ስልቶች በተለያዩ ማራኪና ጠቃሚ ዘዴዎች መተካት ይገባል። ይህንንም ለማሳካት መምህሩ ለጥሩ አንባቢነት የሚያበቁ መሠረታዊ ባሕርያትን ከገሃዱ ዓለም ንባብ እያስሰና እየቀነጨበ ለትምህርቱ ማጠናከሪያነት ማዋል ይጠበቅበታል። ይህ ሲሆን ትምህርቱ በክፍል ውስጥ ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር ከመርዳቱም በላይ ተማሪዎቹ የቀሰሙትን ዕውቀት ከዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት ያስችላል።

ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ ማለትም የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን በመጠቀምና ቅንጫቢ ጽሑፎችን ወደክፍል በማምጣት ወይም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ምንባቦችን ጠንካራና ደካማ ጎን በመገምገም ለደረጃው እንዲመጥን አለዝቦ በማቅረብ የንባብ ትምህርት ዓላማ ግቡን እንዲመታ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ደረጃውን በመጠነ መልኩ የሠለጠኑ፣ስለንባብ ትምህርት ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው ብቁ የቋንቋ መምህራን መኖራቸው ግድ ይላል።

## 1.2 አነሳሽ ችግር

አጥኚው ይህን ጥናት እንዲያጠና ያነሳሳው ከዚህ በፊት በማስተማር ሥራ ላይ በቆየበት ወቅት በአካባቢው በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የቋንቋ መምህራንን ለመገምገም እድል አግኝቶ የነበረ ሲሆን በወቅቱም በተለይም የንባብ ትምህርትን በተመለከተ መምህራኑ በመማሪያ መጽሐፍ ላይ ጥገኛ ከመሆናቸው ባሻገር የምንባቦች አቀራረብም አብዛኛውን በመምህሩና በተማሪዎች ከፍ ባለ ድምጽ ማንበብ ላይ የተመሠረተ ነበር። ይህ አካሄድ ደግሞ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ከማነሳሳትና ክሂላቸውን ከማጎልበት አንፃር ሲታይ የሚኖረው ፋይዳ በጣም ውስን ነው። ይህም ሁኔታ ዘወትር በአጥኚው አዕምሮ ውስጥ የሚመላለስ ሀሳብ በመሆኑ አሁን ባገኘው መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ጥናቱን ለማከናወን ተነሳስቷል።

በመጨረሻም በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ በቡለን ወረዳ ስምንተኛ ክፍልን በሚያስተምሩ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የአንብቦ መረዳት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ምን እንደሚመስል መመርመሩ ተገቢ ነው። ከዚህም በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳል፤

- ❖ መምህራኑ አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ረገድ ዘመናዊ አቀራረብ ዘዴን ይከተላሉ?
- ❖ በዘመናዊ የአንብቦ መረዳት አተገባበር ላይ እንቅፋት የሚሆኑት ችግሮች ምንድናቸው?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

በቡለን ወረዳ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ስምንተኛ ክፍልን በሚስተምሩ ትምህርት ቤቶች የአንብቦ መረዳት ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ምን ይመስላል የሚለውን ለማጥናት ነው። ከዚህኛው ዋና አላማ ላይ ለመድረስም ይህ ጥናት የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ይዞ ተነስቷል። ከአንብቦ መረዳት ትምህርት ደረጃዎች ትግበራ፣ ጥያቄዎች፣ ስልቶች፣ ከመምህራን ሚናና ግንዛቤ አንፃር፤

- ❖ በክፍል ውስጥ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ተግባራዊ የሚደረገውን ዘዴና አቀራረብ መለየትና ተገቢነቱን መፈተሽ፣
- ❖ በክፍል ውስጥ ትግበራ ላይ ያሉትን ችግሮች መለየት እና

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በአንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ የአንብቦ መረዳት ትምህርቶች ከዘመናዊ አቀራረብ ዘዴ አንጻር ስለሚፈትሽ መምህራኑ ዘመናዊ የንባብ ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ከማድረጉም ባሻገር ለተግባራዊ እንቅስቃሴ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ሊያበረታታቸው ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ ይህ ጥናት፡-

- የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ የተሻለውን መንገድ በመጠቀም አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍትን ለሚያዘጋጁ ተቋማትና ግለሰቦች፤
- ተመሳሳይ ጥናት ለሚያካሄዱ አጥኚዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል የአጥኚው እምነት ነው፡፡

## 1.5 የጥናቱ ገድብ

የንባብ ክሂል ትምህርት በሁሉም የክፍል ደረጃዎች የተለያዩ ዓላማዎችን መሰረት ባደረገ መልኩ እንደሚሰጥ ግልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጥናት በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሶስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አተገባበር መፈተሽ ላይ እንዲያተኩር ተደርጓል፡፡ ይህም የተደረገው በዋናነት ጥናቱ ይዞት የተነሳው የክፍል ውስጥ አተገባበርን በመፈተሽ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ከአላማው ላለመውጣት ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ካለው የገንዘብና የጊዜ እጥረት ሁሉንም የንባብ ትምህርት ክንውኖች ለመፈተሽ አስቸጋሪ ስለሚሆን ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም የግል ትምህርት ቤቶች እንዳይካተቱ ተደርጓል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል የማስተማሪያ መሳሪያ፣ የመምህራን የስልጠና ደረጃና የመማሪያ ክፍል ስፋት ከተማሪዎች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝነት፣ ወዘተ. ልዩነት ሊኖረው ስለሚችል በትምህርቱ አቀራረብ ላይም ልዩነት ሊፈጥር ይችላል፡፡ ስለዚህ እነዚህን ተላውጦዎች ለመቆጣጠር ይረዳ ዘንድ የግል ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ መረጃዎች የሚሰበሰቡትም በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ የ8ተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ብቻ ሲሆን ሌሎች መምህራንና በሌላ የክፍል ደረጃ

የሚገኙ ተማሪዎች በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም። ይህም የተደረገው ስራው ውጤታማ ይሆን ዘንድ መረጃውን በዋናነት ከሚመለከታቸው አካላት መሰብሰብ የተሻለ ስለሚሆን ነው። ከዚህም በተጨማሪ ይህ ጥናት በዋናነት በአንብቦ መረዳት ጥያቄ ደረጃዎች ትምህርት፣ ስልቶችና በትግበራው ሂደትም የመምህራን ሚናና ግንዛቤ ወዘተ. ላይ የሚያተኩር ሲሆን የአንብቦ መረዳት ፈተናዎች፣ በመምህሩ መምሪያና በስርዓተ ትምህርቱ ላይ አያተኩርም።

## 1.6 ያጋጠሙ ችግሮች

ይህ ጥናት ከተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ በመምህራን የሚሞላው የጽሑፍ መጠይቅ አንዱ ነው። ይህም የጽሑፍ መጠይቅ በተተኳሪ መምህራን እንዲሞላ የተደረገ ሲሆ የተበተኑት መጠይቆችም በሙሉ ተሞልተው ተመልሰዋል። ይሁን እንጂ ከተሞሉት የጽሑፍ መጠይቆች ውስጥ የተወሰኑት መምህራን ያልሞሏቸው ውሰን ጥያቄዎች ነበሩ። እነዚህም በጥናቱ ውጤት ላይ ልዩነት ሊፈጥሩ ስለሚችሉ በትንተናው ውስጥ እንዳይካተቱ ተደርገዋል።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳን

## 2.1 የንባብ ምንነት

ስለንባብ ምንነት የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ የተለያየ ብያኔ ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡ Harris and Sipay (1990:9) እንደሚሉት፣ንባብ በአዕምሮአችን ውስጥ በፍጥነትና በግል የሚከናወን አዕምሯዊ ተግባር ስለሆነ ለንባብ የሚሰጧቸው ብያኔዎች የተለያዩ ሁነው እናገኛቸዋለን፡፡ እንዲህ ሲባል ግን የሚሰጡት ብያኔዎች ፈራቸውን የለቀቁ ናቸው ለማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ብዙዎቹ ግን (ለምሳሌ፡- Silberstien, 1994 XI, Grant, 1989: 60; Weaver, 1976:22) ንባብ ውስብስብ ሂደት ስለመሆኑ ከመግለጽ አልተቆጠቡም፡፡ Mc Yun, (1995:180) "ንባብ ጥርጣሬን ለመቀነስ የሚደረግ ሂደት ነው" ሲሉት (Wallace, 1993:4) ደግሞ በበኩላቸው "ከአንድ ጽሑፍ ጋር ተግባቦትን ለመፍጠር እንደመተርጎሚያ መንገድ የምንጠቀምበት ነው" በማለት ይገልጹታል፡፡ ብዙዎችም (ለምሳሌ፡- Harris, and Sipay, 1990:10 Ur, 1996: 14) ንባብ ከአንድ ጽሑፍ መልዕክት መገዘዞ ማውጣት ማለት እንደሆነ ይበይኑታል፡፡

ንባብን በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን ከላይ የተሰጡት ብያኔዎች አንድን የንባብ ገፅታ መሠረት ያደረጉ በመሆናቸው ውስንነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ንባብ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ለተለያዩ ዓላማዎች ስለሚከወን ከሞላ ጎደል ሁሉን ሊዳስስ የሚችል ብያኔ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህም አኳያ Nattall (1988:2) ንባብን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በይነውታል፡፡ ይኸውም ንባብ አንድን ጽሑፍ መረዳት፣ ፊደላትን መለየት፣ መቁጠርና ድምጽን ማፍለቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ፊደልን ሳይለዩ ንባብን መጀመር አይቻልም፡፡ የንባብ መጀመሪያ የፊደላት ልየታ እንደሆነም ግልጽ ነው፡፡ ከንባብ ትምህርት አኳያም በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ቀናት የሚከናወን ይሆናል፡፡ ንበትን ለማለማመድ፣ ሀፍረትን ለማስወገድ፣ የተጻፈን ጽሑፍ በቃል በማንበብ መልዕክት ማስተላለፍ ፣ በኑባሪያዊው ዓውድ ያለ ክስተት በመሆኑ፣ እነዚህን ለማለማመድ በሚሉ ዓላማዎች ተማሪዎች የቃል ንባብ እንዲያከናውኑ ይደረጋል፡፡ ስለዚህ ከፊደል እስከ ጽሑፍ ያሉትን ወደ ድምጻዊ አቻቸው መተርጎም አንዱ የንባብ ብያኔ እንደሆነ መገንዘብ ያሻል፡፡

በሌላ መልኩም ንባብ ውስብስብና ቅንጅት የሚታይባቸው ብዙ ንኡስ ሂደቶችን የሚያካትት ነው (Gough, Hoover, and Pterson, 1996:1) ተብሎ ሊበየን ይችላል። ንባብ ፊደላትን በመለየት ይጀምራል። የዐይን እንቅስቃሴው ወደ ሌሎች ፊደላት ስለሚያመራ በመቀጠል የቃላት ልየታ ይከሰታል። ተራ የቃላት ልየታ በቂ ስላልሆነ ሂደቱ ወደቃላት ፍቺ መወሰን ያመራል። የቃላት ፍቺ አሻሚ ስለሆነ አንባቢ አሻሚነትን ለማስወገድ ይጥራል። የእያንዳንዱ ቃል ተገቢው ፍቺ ከተለየ በኋላ ቃላቱን ያቀናጃቸዋል። ከዚህ በኋላ የዐረፍተነገሩን ፍቺ ለመወሰን የአንባቢው ዕውቀት ታክሎበት ከቀዳሚዎቹ ዐረፍተነገሮች ፍቺ ጋር ዝምድና እየፈጠረ ተረድኦት ይከሰታል።

Williams (1984) በበኩሉ፣ ንባብ አንድን በጽሑፍ መልክ የቀረበን ሐሳብ የማስተዋልና በትክክል የመገንዘብ ሂደት ነው ይለዋል። ከዚህም ንባብ ጽሑፉን በተወሰነ ፍጥነት አንብቦ ከዳር እስከዳር ከመውጣት ደረጃ ያለፈ (የተለየና የበለጠ) እና በጽሑፍ አማካይነት ሊገለጽ የተፈለገን አንድ ሐሳብ ወይም መረጃ ለመጨበጥ በጥንቃቄ የሚተገበር ሂደት እንደሆነ እንገነዘባለን፤ ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው አንብቦ መረዳት አንዱና ዋነኛው የንባብ ክፍል እንደሆነ ነው። ቀጥለንም ይህንን የንባብ ክፍል እናያለን፤

## 2.2 አንብቦ መረዳት ምንድን ነው?

በመስኩ የሚገኙ ምሁራን አንብቦ መረዳትን የሚገልጹበት መንገድ፣ ምንም እንኳ የተለያየ ቢሆንም፣ ጥልቅ ማሰብን የሚሻና የመጨረሻ ግቡም ተረድኦት የሆነ የንባብ ዘርፍ ነው ብሎ ማጠቃለል ግን ይቻላል። Smith (1985) አንብቦ መረዳትን ሲገልጹ፣ አንድ አንባቢ ይሂቸው ለሚነሳ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ማለት ነው ይላሉ። እንደገለጸውም አንድ የሚነበብን ጽሑፍ በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማንሳት የማንኛውም የአንብቦ መረዳት ንባብ ባሕሪይ ነው። አንባቢው ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ አገኘ ማለት በአንባቢውና በጸሐፊው መካከል ተግባቦት መኖሩን ያመለክታል በአንባቢውና በጸሐፊውም መካከል ጥሩ ተግባቦት የሚኖረውም ተረድኦት ሲኖር ነው። ባጭሩ አንብቦ መረዳት ማለት ካንድ ምንባብ የተፈለገውን መረጃ ለይቶ ማውጣት መቻል ነው ብሎ መግለጽ ይቻላል።

አንብቦ መረዳት በአንድ ምንባብ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ከመገንዘብ ባለፈ ጠቃሚና አዳዲስ መረጃዎችን ለይቶ ለማውጣት የሚያስችል ሂደት እንደሆነም መገንዘብ ያሻል።

ይህም የተፈለገውን መረጃ ለይቶ ማውጣት፤ ያልተፈለገውን ደግሞ መተውን ያጠቃልላል። ይህንንም በሚከተለው አባባል ማረጋገጥ ይችላል፤

*አንብቦ መረዳት ከአንድ ጽሑፍ የሚፈልገውን መረጃ ለይቶ ማውጣትን የሚያጠቃልል አንድን ጽሑፍ የመገንዘብ ሂደት ነው። አንባቢ በተገቢ ፍጥነት ተፈላጊውን መረጃ የሚያወጣበት፤ የማያስፈልገውንም የሚተውበትና ከተራ ግንዛቤ ያለፉ ጥልቅ ግንዛቤን ይመለከታል* (Grellet, 1981:3)።

በአንብቦ መረዳት ሂደት ከአንድ ጽሑፍ የሚፈለገውን መልዕክት መዝዞ ለማውጣት ሲባል ንባብን ማካሄድ ግድ ይላል። ከጽሑፍ የምናወጣው መልዕክትም በቀላሉ ላይገኝ እንደሚችልም ሊታወቅ ይገባል። ማለትም አብዛኛውን ጊዜ ፀሐፊዎች ለማስተላለፍ የሚፈለጉትን ጉዳዮች በቀጥታ የመግለፅ ባሕሪይ ላይታይባቸው ይችላል። ለዚህም ነው አንብቦ መረዳት ከተራ ግንዛቤ ያለፈ ጥልቅ ግንዛቤን የሚጠይቅ ሂደት ነው የሚባለው።

አንድ አንባቢ ከሚያደርገው ንቁና ውስጣዊ ተሳትፎ በመነሳት አንድን ጽሑፍ መገንዘብ የሚችለው በንባብ ጊዜ የቋንቋ ችሎታውን፣ ዳራዊ ዕውቀቱንና የጽሑፍን ግብአት ሲጠቀም ብቻ ነው። Smith (1985:14) በጥቅሉ እንደሚያቀርቡት አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት የሚታይ መረጃ/ከምንባቡ የሚገኝ መረጃ/ እና የማይታይ መረጃ /ከርዕሱ ጋር ያለን ትውውቅ፣ የንባብ አጠቃላይ ችሎታ፣ ያለን ቀደምት ዕውቀት/ ያስፈልጋል። በተለይ የማይታዩ መረጃዎች አስፈላጊነት ጎልቶ እንዲታይ የሚያደርጉ ሁለት ዓበይት ምክንያቶች አሉ (Smith 1985: 75)።

- ❖ ንባብ ጽሑፋዊ ምልክቶችን ወደ አቻ ድምጾች የመቀየር ተግባር ብቻ አይደለም።
- ❖ መልዕክት ሊቀርብ የሚችለው በላዕላይ መዋቅር ብቻ ሳይሆን ቀደምት ዕውቀትንና የቴክስቱን ቋንቋ በሚጠይቀው ታህታይ መዋቅር ጭምርም ነው።

በተለይም ውጤታማ ንባብ ሥነ-ልቦናዊ ሥነ-ልሣን ሞዴሎች መሠረት ባደረገ መልኩ ሲበየን እናስተውላለን ሚዮን(Mie-yun, 1995, 180) ጉድማንን (Goodman, 1982) በመጥቀስ። ንባብን በሐሳብና በቋንቋ መካከል ያለውን መስተጋብር የሚያካትት "የሥነ-ልቦናዊ ሥነልሳን ግምታዊ ጨዋታ" ነው በማለት ይገልጹታል። ውጤታማ አንባቢ የምንለው የሚያነበውን ጽሑፍ አጠቃላይ መልዕክት በተወሰኑ አንቀጾች ንባብ ይተነብያል። በንባብ ሂደት ጊዜ የትንበያውን ትክክለኛነት ይፈትሻል፤ በመጨረሻም

ያረጋግጣል። ስለዚህ ውጤታማ ንባብ የምንለው የንሞና፣ የትንበያ፣ የሙከራና የማረጋገጫ ደረጃዎችን የሚያካትት ሂደት እንደሆነ ማጠቃለል ይቻላል። እዚህ ላይ “ግምት” ሲባል አንባቢ ከባዶ ተነስቶ የመሰለውን የሚተነብይበት ደረጃ እንዳልሆነ ግልጽ መሆን አለበት። ግምቱ በነሲብ የሚከናወን አይደለም። ለግምቱ መነሻ በመሆኑ ሁለት ምንጮች/ምንባቡና አንባቢ በጽሑፉ ላይ የሚያክለው ነገር/ ላይ የተመሠረተ በመርሕ ላይ የተሞረከዘ ግምት ነው (Williams, 1984:3)።

በሌላ በኩል ከአንድ ጽሑፍ ተፈላጊውን መልዕክት ለይቶ ማውጣት የሚቻለው በአንባቢና በጽሑፍ መካከል በሚካሄድ “ድርድር” ነው ልንል እንችላለን። “ድርድሩም” የተለያዩ ግብዓቶችንና ዕውቀትን የሚጠይቅ ሆኖ ይገኛል። አንባቢ ዕውቀቱንና የጽሑፉን መረጃ ካልተጠቀመ አንድን ጽሑፍ አንብቦ መረዳት ይችላል ለማለት ይከብዳል። ለዚህም ነው አንብቦ መረዳት በአንባቢውና ቋንቋን ለመወከል በሚያገለግሉ ጽሑፋዊ ምልክቶች ልየታና ግንዛቤ፣ ሥነ-ልሳናዊ መረጃ፣ አዕምሮታዊ ክሂሎችና፣ በውሱን ርዕስና ስለአካባቢያችን ያለን እውቀት መካከል ያሉ መስተጋብሮች ውጤት ነው (Harris, and Sipay 1990:10) የሚባለው።

በአንብቦ መረዳት ሂደት ውስጥ የሥነ-ልሳናዊ ኢ-ሥነልሳናዊ ወይም የሚታዩና የማይታዩ መረጃዎች ቅንጅት የግድ ሲሆን የመረጃዎች አለመኖር፣ መዳከም ወይም ቅንጅት የላላ መሆን አንብቦ መረዳትን ሊያደናቅፍ እንደሚችል መገመት አያዳግትም። እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ ቢኖር የአንብቦ መረዳት ደረጃና ምሉእነት የሚመሠረተው የምንፈልገውን መረጃ ለማውጣት ለአንብቦ መረዳት የሚያስፈልጉ ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች አንባቢው አሟልቶ በመገኘቱ ብቻ ሳይሆን አንባቢው ክሂሎቹንና እውቀቱን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል በመቻሉም ጭምር ነው። ስለዚህ በአጠቃላይ አንብቦ መረዳት የአንድን ጽሑፍ መልዕክት መረዳትንና ወደ መረዳት የሚያመሩ ክሂሎችንና ዕውቀትን የሚጠይቅ የንባብ ትምህርት ዋነኛ ግብ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

## 2.3 የንባብ ትምህርት ዓላማዎች

በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የንባብ ትምህርት ዓላማ የጽሑፎችን መልዕክት የመረዳት ችሎታ ለማዳበር፣ በንባብ አጠቃላይ እውቀትን እንዲጨምሩ ለመረዳት፣ ከተለያዩ የንባብ ባህሪያት ጋር ለመተዋወቅና የሂሳዊ ንባብን ችሎታ ለማዳበር እንደሆነ ከዊልያም (William 1984:19)ና ከግራንት (Grant,1990:60) ድርሳናት መረዳት ይቻላል:: ይሁን እንጂ እነዚህ የንባብ ትምህርት ዓላማዎች ውስንነት የሚታይባቸው እንደሆኑ መገመት አያዳግትም:: እንደ Herris and Sipay (1990: 95-95) ትንተና የንባብ ትምህርት ዓላማዎች ተማሪዎች ንባብን እንዲማሩ፣ በንባብ መረጃ ማውጣትን እንዲችሉና ለመዝናናት ማንበብን እንዲችሉ ከማድረግ የሚያንሱ ወይም የሚበልጡ አይሆኑም:: እነዚህን ዓላማዎች ለማስፈፀም የንባብ ትምህርቱ ሦስት ዓይነት የንባብ ዓይነቶችና ተግባራትን የሚያጠቃልል መሆን አለበት፤

1. እድገታዊ ንባብ፡- ይህ ዓይነቱ ንባብ የንባብ ክሂሎችና ስልቶችን ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራትን የሚያካትት ነው:: በሌላ አባባል መሰረታዊ ወይም አቀላጣፊ ክሂሎችንና አንብቦ መረዳትን ለማዳበር ጥቅም ላይ ይውላል::
2. አገልግሎታዊ ንባብ፡- ይህ ንባብ መረጃዎችን ማውጣት ዋና ዓላማቸው ያደረጉ ንባቦችን ሁሉ ይመለከታል::
3. የመዝናናት ንባብ፡- መዝናናትን፣ ደስታ መጎናፀፍንና መደነቅን ዋና ዓላማዎቻቸው የሚያደርጉ ተግባራትን የሚያካትት ንባብ ነው:: የተግባራቱ ዓላማ የንባብ ዝንባሌን ለማሳየት፣ የንባብ ዝንባሌን ለማዳበርና ለማሻሻል ወይም ሥነ-ጽሑፋዊ ሂስንና ጣዕምን ለማጥራት ሊሆን ይችላል Herris and Sipay (1990: 95-95) ::

ጤናማና አስተማማኝ የንባብ ትምህርት እንዲኖር ከተፈለገ ግልጽና ተገቢ ግቦችን መቅረጽ የመጀመሪያው ደረጃ ሊሆን ይገባል:: ከዚህ ዓንፃርም የቋንቋ መምህራን ስለንባብ ትምህርት ዓላማ ግልጽ ግንዛቤ የግድ የሚያስፈልጋቸው ይሆናል:: አንብቦ መረዳትን ማስተማር ሲታሰብ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ዓላማዎችን ይዞ የሚነሣ መምህር ዓላማዎቹን ለመተግበር የተለያዩ መንገዶችን ስለሚጠቀም ትምህርቱን ውጤታማ እንደሚያደርገው ይታመናል::

Williams (1984:13) የንባብ ትምህርት ዓላማዎች ተማሪዎች የሚከተሉትን ነገሮች እንዲጨብጡ ያስችሏቸዋል ይላሉ፤

1. መሠረታዊ የሆነ የንባብ ዕውቀትን እንዲጨብጡና ማንኛውንም ነገር አንብበው ይዘቱን እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል፡፡
2. በእውነተኛው ሕይወት (Real life) ሊተገበር የሚችል የንባብ ክህሎት እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡
3. ተማሪዎች ዓላማቸውን ማዕከል ባደረገ መልኩ የተለያዩ የአነባብ ስልቶች እንዲለምዱ ያደርጋቸዋል፡፡
4. ተማሪዎች የዕውቀት አድማሳቸውንና የቋንቋ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ የንባብ ትምህርት ዓላማ የተማሪዎችን በፍጥነትና በትክክል ያለችግር የማንበብና የመረዳት ችሎታ እንዲሁም የንባብ ልምድን ለማዳበር የሚያስችል ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህም አንጻር፣ ተማሪዎች የንበብን ክሂል ምንነት፣ ዓይነት፣ ባሕርያት፣ ጥቅምና ኀዑሳን ክሂሎች በሚገባ ማወቃቸው የንባብ ችሎታቸውን የበለጠ ለማሻሻል በትጋት ንባብን እንዲለማመዱ ሊያነሳሳቸው ስለሚችል ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

## 2.4 የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ

ተማሪዎች የንባብ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ያመች ዘንድ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርቱ የየራሳቸው ዓላማዎችና ባሕሪያት ባሏቸው በቅድመ ንባብ (Pre-reading)፣ በንባብ ጊዜና(While-reading) በድህረ ንባብ (post-reading) ደረጃዎች ተከፍሎ መስጠት አለበት (William, 1984:37; Rosa Maria, Merarivas 1999:15: Dubin and Bycina,1991:202)::

### 2.4.1 የቅድመ ንባብ ትምህርት

ይህ ደረጃ መምህሩ ትምህርቱ ሲጀመር ተማሪዎችን ለንባብ የሚያዘጋጅበት ማለትም ዋናውንና ቀጣዩን የንባብ ትምህርት፤ የንባብ ጊዜ ትምህርት በተገቢው መንገድ እንዲከታተሉት ትኩረታቸውም ተሰብስቦ ወደ ትምህርቱ እንዲሆን በማድረግ ምንባቡን እንደረዱት፤ አጠቃላይ ስነ ልቦናዊና ሥነ-ልሳናዊ ዝግጅት እንዲኖራቸው ለማድረግ

የተለያዩ ተግባራት የሚያከናወንበት ነው። Harmer (1990:151) ይህ ደረጃ ተማሪዎችና መምህራን ለዋናው ትምህርት ራሳቸውን የሚያዘጋጁበትና ከምንባቡ ጋር የሚተዋወቁበት ትምህርት ነው በማለት ይገልጹታል። ይህንን ለማድረግም በሚከተሉት ዓላማዎች ላይ መመስረት ይገባል፤

1. ተማሪዎች የሚያነቡበትን ምክንያትና እንዴት እንደሚያቡ እንዲያውቁ በማድረግ የማንበብ ፍላጎታቸውን ለመቀስቀስ፣
2. ተማሪዎች በንባብ ጊዜ ሊገጥሟቸው የሚችሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን መቋቋም እንዲችሉ ለማዘጋጀት እና
3. ተማሪዎች ያሏቸውን ቀደምት ዕውቀት ከሚያነቡት አዲስ ይዘት ጋር እንዲያያይዙ ለማነሳሳት የሚሉት ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የቅድመ ንባብ ትምህርት ዓላማዎች ናቸው ሲባል በማንኛውም የቅድመ-ንባብ ትምህርት የግድ ሊተገበሩ ይገባል መባል እንደሌለበት ሊታወቅ ይገባል። ስለሆነም የቅድመ ንባብ ዓላማዎችን ለመወሰንና ተገቢ ተግባራትን ለመጠቀም የመምህራኑ ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም። Harris and Sipay (1990:557) የቋንቋ መምህራን ሚና ምን ሊሆን እንደሚችል በሚከተለው መንገድ ይገልጹታል፤

መምህሩ የንባብ ትምህርትን ለማስተማር ሲያቅድ ምንባቡን ለመረዳት የትኞቹ እሳቤዎችና የትኞቹ የእሳቤ ዝምድናዎች ጠቃሚ እንደሆኑ፣ጸሐፊው ምን ዓይነት እሳቤዎችን እንዳቀረበ፣ ምን ያህል ግልጽነት እንዳላቸውና የትኞቹ እሳቢዎችና ዝምድናዎች በተማሪዎች ላይ ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉት የሚለውን ለመወሰን ምንባቡን አስቀድሞ ማንበብ ይኖርበታል።

በተነሳስኦትና በንባብ ትምህርት መካከል የጠበቀ ዝምድና እንዳለ ግልጽ ነው። ስለሆነም አንብቦ መረዳትን ማስተማር ሲታሰብ ተነሳስኦት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ተማሪዎች ምንባቡ የሚገኝበትን ገጽ እንዲገልጡና ምንባቡን ካነበቡ በኋላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ በማድረግ የንባብ ትምህርትን የሚጀምር መምህር ለተነሳስኦት ትኩረት እንዳልሰጠ መገመት አያዳግትም (Williams,1986:37)። ተማሪዎች አናኗራቸውንና ስሜታቸውን የሚነካ ነገር ካገኙ ስለነገሩ ያስባሉ፤ ይወደያሉ፤

መጨረሻውን ለማየትም ይጓጓሉ፡፡ ግሪሌትም (Grellet, 1981:18) ለአንብቦ መረዳት ትምህርት የተነሳስኦትን አስፈላጊነት እንደሚከተለው ይገልጹታል፤

አንድ ጽሑፍ ለማንበብ ተነሳስኦት የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ የምናነበው ነገር የፈለግነውን ማንበብ ይሆናል፤ መነሳሳት ማለት ደግሞ ከአንድ ምንባብ የተለያዩ መረጃዎችን ለማውጣት ዝግጁ መሆን ማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ለሚያነሷቸው የተለያዩ ጥያቄዎች መልስ፣ ፍላጎታቸውን ባነሳሱት ጉዳዮች ዙሪያ ደግሞ መረጃዎችን ፍለጋ ላይ ያነጣጥራሉ፡፡ ከጽሑፍ አንዳች ነገር መጠበቅ ደግሞ የማንኛውም ንባብ ባህሪይ ነው፡፡

ስለዚህ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ሂደት የመጀመሪያው ተገቢ እርምጃ የተማሪዎችን ፍላጎትና ዝንባሌ መፈተሽ ይሆናል፡ ነገር ግን የሁሉንም ተማሪ ፍላጎት ለይቶ ማወቅ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ በጥቅሉ ግን የቋንቋ መምህር ሊገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ይኖራል፡፡ ምክንያቱም ግንዛቤ ካለ ተማሪዎችን ለማነሳሳት ቢያንስ አንድ እርምጃ ለመራመድ ያስችላልና፡፡ እንደ Gebhard (1999:213) አባባል ሰዎች ሲማሩ የሚማሩት ነገር የማይናቅ ጠቀሜታ ካለው፣ ከኑሯቸው ጋር የተቆራኘና ተግባራዊ የሚያደርጉት ከሆነ በጥሩ ሁኔታ ይከታተሉታል፡፡ በአጠቃላይ መነሳሳት ካለ የንባብ ልምድን ማዳበር ይቀላል (Nttall, 1983:30)፡፡

በአንብቦ መረዳት የትምህርት ሂደት የቅድመ ንባብ ትምህርትን ማከናወን የሚቻለው ተገቢ የሆኑ የቅድመ ንባብ ተግባራትንና ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ይሆናል፡፡ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ተግባራትም ሆኑ ጥያቄዎች የተማሪውን የአንብቦ መረዳት ደረጃ የሚጨምሩ ስለመሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ የንባብ ትምህርት ውጤታማ እንዲሆን ከማስቻል አንጻርም ትንበያ፣ ውይይት፣ የተለያዩ ስዕሎችን መጠቀም፣ ርዕስ መተንተን ምንባብ ማስተዋወቅ፣ የቃላት ፍቺ መገመት፣ ቁልፍ ቃላትን ማስተዋወቅ፣ ሀሳብ ማመንጨት ወዘተ. የመሳሰሉት ተገቢ የቅድመ ንባብ ተግባራት እንደሆኑ (Harmer 1990) ይገልጻሉ፡፡

### 2.4.2 የንባብ ጊዜ ትምህርት

የንባብ ጊዜ ትምህርት  አጠቃላይ ዓላማ ራስ - መር በሆነ መልኩ ንቁ ተሳታፊ የሆኑ አንባቢ ተማሪዎችን መፍጠር ሲሆን ይህንን ከግብ ላይ ለማድረስ  የሚያስችሉ ዝርዝር ዓላማዎችም ይኖሩታል። እነሱም፡- የምንባቡን አጠቃላይ ይዘት እንዲገነዘቡ፣ የምንባቡን መዋቅር እንዲተነትኑና የደራሲውን ዓላማ እንዲገነዘቡ ለመረዳት ነው። የንባብ ጊዜ ትምህርት  ቀዳሚው ክንውን አንድን ጽሑፍ ማንበብ  ነው። ስለዚህ የሚከተለውን ስነልቦናዊ ስነልሳን ሞዴሎች መሰረት ያደረገ አቀራረብ በመከተል  ተማሪዎች እንዲያነቡ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፤




**(MeiYun,1995-187)**

አብዛኛውን ጊዜ ጸሐፊዎች የሚጽፉት እንዲነበብላቸው እንጂ እንዲደመጥላቸው ስላልሆነ ንባብ በዝምታና በግል ሊነበብ ይገባዋል(Greenwood, 1992)። ይህንንም ሁኔታ ወደ መማሪያ ክፍል ስናመጣ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ተግባር ላይ የሚውል ምንባብ በዝምታና በግል መነበብ እንደሚገባው የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ።Swafar,Arens and Byrens (1991:22) የ Bernhardt (1983:113)ን ግኝት  ጠቅሰው እንዳቀረቡት የዝምታ ንባብ ከቃል ንባብ በተሻለ መንገድ ተማሪዎች የግላቸውን ስልት እየተጠቀሙ አንድን ጽሁፍ  አንብበው ለመረዳት እንዲችሉና ትምህርቱ ላይም ትኩረታቸው እንዲያርፍ ያስችላል።  ይህ ጊዜንና ጉልበትን ለመቆጠብና አንድን ጽሑፍ በሚፈለገው ፍጥነት ለመረዳት የሚያስችለው የንባብ አቀራረብ (Harris, and Sipay, 1990:102; Pahuja, 2002: 177) የቃላት  ልየታና ንበት የመሳሰሉት ንዑስ ክሂሎች መሻሻልን ለመከታተል፤ ለተውኔታዊና ማራኪ ታሪኮች አቀራረብ ልምምድ እንደመሣሪያነት የሚያገለግለውና ዐይናፋርነትን ለመቀነስ ተገቢ ከሆነው የቃል ንባብ  የራሱ የሆኑ ዓላማዎች እንዳሉት ሊታወቅ ይገባል። እንዲህ ሲባል ግን የቃል ንባብ (oral reading) በተለይ በሁለተኛ ደረጃ

ክፍሎች አያስፈልግም ለማለት አይደለም፡፡ የዝምታ ንባብና የቃል ንባብ የተለያዩ ባሕርያት፣ጠቀሜታዎችና ዓላማዎች ስላሉዋቸው ከሚቀርቡት የንባብ ትምህርቶች ጋር ተጣጥመው መቅረብ አለባቸው፡፡

ንባብን በማስተማር ሂደት የተለያዩ ጥያቄዎች ለተለያየ ዓላማ ተግባር ላይ እንደሚውሉ የሚታወቅ ሲሆን ይኸውም፡- ከንባብ በፊት፣ እየተነበበ ሳለ ወይም ንባቡ እንደተጠናቀቀ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ጥያቄዎች መቼ መቅረብ እንዳለባቸው የሚወሰነው ግን በአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ዓላማ ነው፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ንባብ መነበብ ከመጀመሩ በፊት የተማሪዎችን ቀደምት ዕውቀት ለመቀስቀስ፣ለመከለስ ወይም ለማሳደግ፣ ወሳኝ የሆኑ እሳቤዎችን ለመቃኘት እንዲችሉ ወይም ለምን እንደሚያነቡ እንዲገነዘቡ ለማድረግ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች (pre-reading question) ሊቀርቡ ይችላሉ (Harris, and Sipay, 1990:571)፡፡ በተለይ ተማሪዎች የሚያነቡበትን ምክንያት እንዲያውቁ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ተማሪዎች ትኩረታቸውን ለማሳረፍና ለማጠናከር ብሎም ተረድኦታቸውን ለማቀላጠፍ የሚኖራቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ መቼ? የት? ማንና ምን? በሚል የሚቀርቡ ጥያቄዎች ደግሞ መረጃዎችን በጥልቀት ፈልቅቆ ለማውጣት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ (Zhenyu,1997:42)፡፡ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በበኩላቸው ቀጥሎ የሚነበበውን ጽሑፍ ይዘት ለመተንበይ፣ ተረድኦትን ለመከታተል፣ የተነበበውን ቀጣይ መረጃ ከቀደምት እውቀት ጋር ለማያያዝ መንገድ የሚመሩ ስለሆኑ ችላ ሊባሉ አይገባም፡፡

ምንባብ ከተነበበ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎች የራሳቸው ባህሪና ጠቀሜታ ያላቸው ሦስተኛ ዓይነት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በዚህ ደረጃ የሚቀርቡ ጥያቄዎችም ተማሪዎች የምንባቡን ዋና ሃሳብ መገንዘብ አለመገንዘባቸውን ለማረጋገጥ፣ ምንባቡን ከተለያዩ ሁኔታዎች አንጻር እንዲገመግሙ የሚያበረታቱ ራሳቸውን በምንባቡ ሁኔታ ውስጥ አስቀምጠው እንዲመለከቱ ለማድረግና የንባብ ክሂልን ከሌሎች ክሂሎች ጋር እንዲያጣምሩ የሚያስችሉ፣ ወዘተ. ስለሆኑ ተገቢ የሆነ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

### 2.4.3 የድኅረ ንባብ ትምህርት

ይህ ደረጃ አጠቃላይ የምንባቡ ይዘት የሚቃኝበትና የማጠናከርያ ሥራም የሚሠራበት ነው፡፡ ይኸውም የተነበበውን ጽሑፍ ማጠቃለልና ምንባቡን ከተማሪዎች ዕውቀት፣

ዝንባሌና አመለካከት ጋር ማዛመድም ዓላማው ነው። በዚህ ደረጃም ተማሪዎች በምንባቡ መነሻነት መስማማት አለመስማማታቸውን እንዲገልጹ በማድረግ የራሳቸውን ፍርድ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። የድኅረ ንባብ ትምህርት ተግባራት ከሚነበበው ጽሑፍ የሚወጡ ቢሆኑም በቀጥታ ምንባቡን የማይመለከቱ ሊሆኑ እንደሚችሉ (Williams, 1990:39) ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።

በጥንታዊ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ሆነ በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የድኅረ ንባብ ትምህርት ጥያቄዎችን የምናገኛቸው አንድ ምንባብ ከቀረበ በኋላ ከሚገኙት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ጋር ነው። የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችና የድህረ ንባብ ጥያቄዎች አንድ ላይ የሚቀርቡበት ሁኔታ እንደሚኖር መለየት አያዳግትም። የቋንቋ መምህሩ ተነሳሽነት ካልታከለበት ይህ አቀራረብ የድህረ ንባብ ትምህርት ላለመስጠት ወይም ላለመኖር መንገድ ሊከፍት እንደሚችል መገመት ይቻላል። ዋናው ቁምነገር የድኅረ ንባብ ትምህርት ጠቀሜታና የተግባራቱን ባሕሪያት ጠንቅቆ በማወቁ ላይ ነው። ስለዚህ የንባብ ትምህርት ደረጃ ተገቢ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ተግባራትም ማጠቃለል፣ ሚና ክንውን፣ ውይይት፣ አስተዋጽኦ መንደፍ፣ ክርክር፣ መዘገብ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ኑባርያዊ ተግባራት ናቸው። እነዚህ ተግባራት ኑባሬያዊ ንባብ አካል ከመሆናቸውም በላይ በክሂሎች መካከል ቅንጅትን ለመፍጠርም ተገቢ ናቸው። ምክንያቱም ንባብ ለብቻው ተነጥሎ የሚገኝ ክሂል አይደለም። የንባብ ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ መቅረቡ ተማሪዎችን የማነሳሳትና የተሟላ የቋንቋ ትምህርት እንዲኖር የመፍቀድ ፋይዳ እንዳለው Byrne (1983) ትንተና መደምደም ይቻላል።

ሦስቱ የንባብ ትምህርት ደረጃዎች በማንኛውም የንባብ ትምህርት የግድ ተግባራዊ መሆን አለባቸው ሊባል አይገባም። በቋንቋ መምህርም እንደ Dubin and Bycina (1991፡204) አገላለጽ ሦስቱን ደረጃዎች የግድ መተግበር እንዳለበት አካል መታየት የለበትም። የቅድመ ንባብ ወይም የድህረ ንባብ ትምህርት ላለማካሄድ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ መካድ አይቻልም። ይሁን እንጂ የሦስቱ የንባብ ትምህርት ደረጃዎች ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ ስላልሆነ ተገቢ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። Williams (1986:40) እንዳመለከቱት ሦስቱ የንባብ ትምህርት ደረጃዎች ሁለት መሠረታዊ ጠቀሜታዎች አሏቸው።ይኸውም፤

ሦስቱን ደረጃዎች ያካተተ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ሁለት አበይት ጠቀሜታዎች አሉት። አንደኛ ፡ ይህ አቀራረብ የተማሪዎች የቋንቋና አካባቢያዊ ዕውቀት አንብቦ መረዳትን ለማፍጠን ጥቅም ላይ እንዲውል በመፍቀድ ተማሪዎች እንዲሳተፉ፣ እንዲነሳሱና እንዲሻሻሉ ያደርጋል። ሁለተኛ ይህ አቀራረብ የንባብ ትምህርት ለብቻው ተለይቶ እንዳይሰጥ የጠበቀ የክሂሎች ቅንጅት እንዲኖር ያስችላል።

ይህም ሊሆን የሚችለው ምንባቦችን በሶስት ደረጃዎች ከፍሎ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ደረጃ በቂና ተገቢ ከሆኑ ተግባራት ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ ሲቻል እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል።

በአንበቦ መረዳት ትምሕርት አቀራረብ ረገድ ስነ-ለቦናዊ ስነ-ልሳን የንባብ ሂደትን የተከተሉ የክፍል ወስጥ ክንዉኖች መኖር አንብቦ መረዳትን በከፍተኛ ደረጃ ሊያዳብር እንደሚችል ይታመናል። ስለዚህ የክፍል ዉስጥ የንባብ ትምህርት አጠቃላይ ዑደታዊ አቀራረብ (Hlistic cyclic approach) ዋና ትኩረቱ የተማሪዎች ትኩረት መልዕክት ላይ እንዲያነጣጥር በሚያስችለው በምንባቡ አጠቃላይ ተረድኦት ላይ ነዉ። አጠቃላይ አቀራረብ የተባለው ከጥቅል ምንባቦች ቅኝት በመጀመር ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በማምራት "ዛፎችን በጫካው አማካይነት ለማየት" ስለሚያስችል፣ ዑደታዊ የተባለዉም የተለያዩ ደረጃዎችን በቅደም ተከተል ስለሚያልፍ ነው Mei-yun (1995:187)።

ባጠቃላይ ትክክለኛው የንባብ ክንውን መረጃ ወይም ደስታ የሚገኝበት ብቻ ተደርጎ የሚታይ ሳይሆን የአንባቢ አመለካከት፣ ገጠመኝ፣ ቀደምት ዕውቀት የሚታከልበትም ጭምር ነው። ይህ የኑባሪያዊ ንባብ ባህሪ በንባብ ትምህርት ወቅትም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። ይህንን እውን ለማድረግም በአንባቢው አዕምሮ ውስጥ ያለውን መረጃ ምንባቡ ውስጥ ካለው መረጃ ጋር ማቀናጀትን የሚጠይቁ ጥያቄዎችንና ተግባራትን በማቅረብ ይሆናል (Williams, 1986:44) ።

## 2.5 የንባብ ትምህርትን በመተግበር ረገድ የቋንቋ መምህራን ሚና

በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን የንባብ ትምህርት ውጤታማ ለማድረግ ዘመናዊ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብን መከተል ተገቢ ነው። ለዚህም መምህራኑ ከስራ ልምዳቸው፣ ከስልጠናና ከወሰዱት ኮርስ ያገኙትን ተሞክሮ መሰረት በማድረግ የማስተማር

ዘዴያቸውን (አቀራረባቸውን) ዘመናዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ምክንያቱም ለተማሪዎች ግልጽ፣ትርጉም ያለውና ከእውነታው ዓለም/ከሕይወታቸው/ ጋር ተያያዥነት ያለው ትምህርት ለመስጠት የቋንቋ መምህራን የንባብ ትምህርትን በተመለከተ ጥልቅ፣ ፍትሃዊ የሆነ ግንዛቤና ዘመናዊ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል። ይህን እውነታ ከንባብ ትምህርት አንጻርም (Brownne,1996:25) "ስለንባብ ትምህርት ሂደት የጠለቀ ግንዛቤ ከኖረ ለተማሪዎች ጊዜያዊና የወደፊት ፍላጎት ተገቢ የሆነ የንባብ ትምህርትን መተግባር ይቻላል" በማለት ይገልጹታል።

የንባብ ትምህርት ሂደትን መገንዘብ መቻል ውጤታማ የንባብ ትምህርትን ለመስጠት አስፈላጊና ዋናው ጉዳይ ስለመሆኑ የሚታመን ሲሆን ብቻውን ግን በቂ እንዳልሆ ብዙ ምሁራን ያስረዳሉ። ጥሩ የንባብ ትምህርት ለመስጠት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል የቋንቋ መምህር የክፍል አያያዝ ተጠቃሽ ሲሆን ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም፣ በመልመጃዎች መካከል ጤናማ ሽግግር እንዲኖር፣ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ የተማሪዎችን ጠባይና ተግባር በቅርብና በተከታታይ ለመቆጣጠር፣ ወዘተ.. እንደሚያስችልና ከተማሪዎች እቅድ ጋር እንደሚያያዝ Harris, and Sipay, (1990:110) ገለፃ መረዳት ይቻላል።

ንባብን በማስተማር ሂደት የቋንቋ መምህራንን ሚና ስናነሳ ሊከተሏቸው የሚችሉትን የአቀራረብ ዓይነቶችን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል። እነዚህም ዘመናዊና ጥንታዊ አቀራረብ በመባል የሚታወቁ ሲሆን በንባብ ትምህርት አቀራረብም የመምህራን ጣልቃ ገብነትና ክፍሉን ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ሚና ጎልቶ የሚታየው በጥንታዊ አቀራረብ ወቅት ነው። በዚሁ አቀራረብ መምህራን ክፍሉን ሙሉ በሙሉ ስለሚቆጣጠሩ ወይም ብዙውን ጊዜ ገለፃ ላይ ስለሚያተኩሩ በትምህርቱ ላይ ጣልቃ በመግባት የተማሪዎችን የንባብ እድገት ያደናቅፋሉ (William,1986)። ዘመናዊ አቀራረብን ተከትሎ ምንባብን የሚያስተምር መምህር የሚኖረው ሚና አንድን የሙዚቃ ኮንሰርት የሚመራ ባለሙያ ሚና ዓይነት ነው። በሌላ አገላለጽ መረጃ በማቀበል ወይም ገለጻ በማድረግ ላይ የተመሰረተ ሚና አይኖረውም ማለት ነው። ባጭሩ ሊኖረው የሚገባው ሚና የክፍል ውስጥ የንባብ ክንውኑን መምራት ብቻ ነው፤ ከዚህም ጋር በተያዘም የተማሪዎች ተነሳስኦት ሊያዳብር በሚችል መልኩ ከተማሪዎች ጋር መልካም ዝምድናን መፍጠር፣

ተገቢ ሙገሳና ሂስ መስጠትንና ከተማሪዎች ትክክለኛ መልስ፣ ጥረትና ከስራቸው ውጤት አንፃር ተገቢ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

ተማሪዎች በመምህራቸው የሚቀርቡላቸው መረጃዎች ቀጥተኛ ተቀባይ ሊሆኑ አይገባቸውም፡፡ በሌላ አገላለጽ ማንኛውንም ነገር ከመምህራቸው የሚቀበሉ መሆን የለባቸውም፡፡ በአንብቦ መረዳት ሂደት ንቁ ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በግላቸው ሃላፊነትን ሊሸከሙ ይገባል፡፡ እንደ Goodman (1986) አባባል ሃላፊነት መውሰድ ማለት ተማሪዎች እርግጠኞች ይሁኑ አይሁኑ የአንድን ምንባብ መልዕክት ለመረዳት መጣርን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ስለዚህ ሃላፊነትን የሚያሸክም ድባብ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ለዚህም መምህሩ ራሱን አሳልፎ መስጠት ይኖርበታል Silberstein (1994)፡፡ ምክንያቱም ማስተማር የቋንቋ ትምህርትን የሚደግፉ እንጂ በእግሩ ቆሞ እንዲሄድ የሚያደርግ አይደለም፡፡

## 2.6 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

በአንብቦ መረዳት ትምህርት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ የተለያዩ ጥያቄዎች የተማሪዎችን ተረድኦት ለመከታተል ብሎም ጥሩ አንባቢ እንዲሆኑ ለማድረግና የምንባቦችን ሃሳብ ግልጽ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ታስበው ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ ጥያቄዎቹም በተቻለ መጠን ከአእምሮታዊ እውነታ ጋር የሚዛመዱ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በኑባሬያዊ ንባብ ወቅት አንባቢዎች የሚኖሯቸውና የሚጠቀሟቸው የንባብ ስልቶች፣ ክሂሎችና ዓላማዎች በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን እንዲያዳብሯቸውና እንዲጠቀሙባቸው ለመረዳት አእምሮታዊ ክሂልን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ተገቢ እንደሆኑ ብዙዎቹ ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ Ericdigest (2000) እንደሚያረጋግጠው በተለይ የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ደረጃዎችን ለማስተማር የሚዘጋጁ ጥያቄዎች የተማሪዎችን አእምሮታዊ ክሂሎችን የሚያዳብሩ መሆን አለባቸው፡፡ ጥያቄዎቹ መካኒካዊ ሂደትን ሳይሆን አእምሮታዊ ሂደትን የሚያነሳሱ መሆን ይኖርባቸዋል (Dudley-Evan,Jony and ST John Maggie,1998:175) በዚህም መሰረት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችና ተግባራት የሚከተሉት ሆነው እናገኛቸዋለን (Sheng,2000:Tollefson,1996:226-227)፡፡

### 2.6.1 ቀጥተኛ ጥያቄዎች

ቀጥተኛ ጥያቄዎች ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ ላይ በቀጥታ የተገለጹትን እንዲያስተውሉ ወይም እንዲለዩ የሚጠይቁና አጫጭር መልሶች የሚሹ ናቸው። መቼ፣ስንት፣ማን፣ የት ወዘተ. የመሳሰሉት አብዛኛውን ጊዜ ቀጥተኛ ጥያቄዎች ናቸው (Mason,1981:81-2)። የሚከተሉትም በቀጥተኛ ጥያቄዎች ስር የሚጠቃለሉ ናቸው፤

- ዝርዝሮችን የመለየት ወይም የማስታወስ ጥያቄዎች
- ዋና ዋና ሀሳቦችን የመለየት ወይም የማስታወስ ጥያቄዎች
- ቅደም ተከተልን የመለየት ወይም የማስታወስ ጥያቄዎች
- ንጽጽርን የመለየት ወይም የማስታወስ ጥያቄዎች
- ምክንያትና ውጤቶችን የመለየት ወይም የማስታወስ ጥያቄዎች
- የገጸ ባህሪያትን ጠባይ የመለየት ወይም የማስታወስ ጥያቄዎች

### 2.6.2 የትንበያ ጥያቄዎች

ጸሐፊዎች ሊያስተላልፉ የፈለጉትን ጉዳይ በግልጽ ሳያስቀምጡ ለአንባቢ የሚተውበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ከአንባቢ የሚጠበቀው የራሱን የማሰብ ችሎታና ቀደምት እውቀትን ተጠቅሞ ሃሳቦችንና ዝምድናቸውን በአንድምታ መረዳት ይሆናል። ይህንንም ተግባር ተማሪዎች እንዲለማመዱ ለማድረግ የሚከተሉት ዓይነት ጥያቄዎች ሊቀርቡ ይገባል፤

- ዝርዝር ሃሳቦችን የመተንበይ ጥያቄዎች
- ዋና ዋና ሃሳቦችን የመተንበይ ጥያቄዎች
- ቅደም ተከተልን የመተንበይ ጥያቄዎች
- ንጽጽሮችን የመተንበይ ጥያቄዎች
- ምክንያት ውጤትን የመተንበይ ጥያቄዎች
- የገጸ ባሕሪን ጠባይ የመተንበይ ጥያቄዎች

### 2.6.3 የግምገማ ጥያቄዎች

ተማሪዎች የአነበቡትን ምንባብ በተመለከተ ሂስ እንዲሰጡ የሚጠይቁ ናቸው። እነዚህም የሚከተሉትን ይመስላሉ፤

- እውነታን ወይም ፈጠራን የመገምገም ጥያቄዎች
- አስተያየትን የመገምገም ጥያቄዎች

- ❖ ብቃትና ተገቢነትን የመገምገም ጥያቄዎች
- ❖ ጠቀሜታን የመገምገም ጥያቄዎች

#### 2.6.4 አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎች

እነዚህ የጥያቄ ዓይነቶች አንድ ምንባብ በተማሪዎች ላይ የሚፈጥራቸው ስነልቦናዊና ስነ ውበታዊ ስሜቶችንና ስነጽሑፋዊ ብልሃቶችን፣ ቅርጾችንና ስልቶችን እንዲሁም ግላዊ ምላሾችን የሚሹ ናቸው። የሚከተሉትም በዚህ ስር ይጠቃለላሉ፤

- ❖ የግል አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎች
- ❖ በቋንቋና በስልት ዙሪያ አስተያየት የመስጠት ጥያቄዎች
- ❖ የደራሲን ምናብ የመተንተን ጥያቄዎች

ባጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመምህር፣ በመማሪያ መጽሐፍ ሊቀርቡ ይችላሉ። ጥያቄዎቹ ግን ከየትም ይሁኑ ክማን አንብቦ መረዳትን ሊያለማምዱ የሚችሉ መሆን አለባቸው። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የሚቀርቡት ጥያቄዎች ከላይ የተጠቀሱትን ባህሪያት ሲላበሱ ነው። ስለሆነም መምህራን፣ አንብቦ መረዳትን ለማለማመድ በመጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎችን ሲጠቀሙም ሆነ ራሳቸው የሚያዘጋጇቸውን ጥያቄዎች በተመለከተ ጥልቅ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል።

## 2.7. የውጤታማ አንባቢ ባሕርያት

### 2.7.1. በዓላማ ማንበብ

አንድን ጽሑፍ ለተወሰነ ጉዳይ ማለትም በዓላማ የማንበብ ልምድ ያለው ሰው ጥሩ አንባቢ ነው ሊባል ይችላል። ይህ ባሕሪይ ያለው ሰውም የሚያነብበትን ምክንያት በቅድሚያ ለይቶ ስለሚያውቅ ከሚያነብበት ምክንያት አንጻር የንባብ ስልቱንና ፍጥነቱን በማስማማት ያነባል Nattall (1982)።

በንባብ ውጤታማ ለመሆን አላማን መሰረት ያደረገ ማንበብን የሚጠይቅ ስለሆነ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነሳሳት አንድን ጽሑፍ የሚያነቡበትን ምክንያት በቅድሚያ ማሳወቅ ይገባል፤ ለዚህም ከንባብ በፊት ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ሥራዎች ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል Nattall (1982)።

## 2.7.2 የመገመት ችሎታ

ጥሩ አንባቢ የቀረበለትን ጽሑፍ ይዘት ቀድሞ በመገመት ስልት ይጠቀማል፡፡ ውጤታማ አንባቢ ስለሚያነበው ጽሑፍ ያለውን ዕውቀት በመጠቀም ከጽሑፍ በመነሣት ምን ሊያገኝ እንደሚችል፣ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል ቀድሞ ይገምትና በንባብ ሂደት ከጽሑፍ የሚያገኘውን ሐሳብ ቀድሞ ከገመተው ሐሳብ ጋር በማዋሃድ አጠቃላይ ግንዛቤ ይወስዳል (Grellet፣ 1981)፡፡

ውጤታማ ንባብ አንባቢው ቀድሞ በገመተውና ለንባብ ባቀረበው ጽሑፍ ሐሳብ መካከል ያለ ተዛምዶን የመመልከት ሂደት ነው (Harmer 1990)፤ ስለዚህ ተማሪዎች አንብቦ የመገንዘብ ችሎታቸውን ለማዳበር ይችሉ ዘንድ የመገመት ክሂላቸው (Predictive skill) የሚዳብርበትን መንገድ መቀየስ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም ከንባብ በፊት ተማሪዎች ቀድመው መገመት የሚያስችላቸውን የተለያዩ ተግባራትን በማቅረብ እንዲከወኑ ማድረግ ያስፈልጋል (Ur, 1996)፡፡

## 2.7.3 ቀደምት ዕውቀትን ለግንዛቤ መጠቀም

ጥሩ አንባቢ የቀረበውን ጽሑፍ በተመለከተ ያለውን ቀደምት ዕውቀት ከሚያነበው ጽሑፍ ውስጥ ከሚገኘው ዕውቀትና መረጃ ጋር በማገናኘት የጽሑፉን አጠቃላይ ይዘት ይገነዘባል (Mei-Yue, 1995)፡፡

ውጤታማ የንባብ ሂደት ቀደምት ዕውቀትን ከቀረበው ጽሑፍ ጋር ማዛመድን የሚሻ ክንውን በመሆኑ (Grellet, 1981) ተማሪዎች ያለፈ ልምድና እውቀታቸውን አንብበው ለመገንዘብ የሚያውሉበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት ማለማመድ ያስፈልጋል፤ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ከቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን ሐሳብ ጽሑፉን መሰረት በማድረግ መገመት እንዲችሉ የሚያደርጉ ተግባራትን ማቅረብ ከመምህሩ ይጠበቃል (Johnsten, 1988)፡፡

## 2.7.4. የቃላትን ፍቺ ከዐውድ መረዳት

ጥሩ አንባቢ በሚያነበው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ፍቺ በሙሉ ለመረዳት ሳይጨነቅ የገቡበትን ዐውድ መሰረት በማድረግና ፍቻቸውን በመገመት አጠቃላይ የምንባቡን ሐሳብ የመገንዘብ ልምድ አለው፡፡ ጥሩ አንባቢ በሚያነብበት ወቅት

የሚገጥሙትን አዳዲስ ቃላት በሙሉ ለማወቅ ሁልጊዜ መዝገበ ቃላት በማገላበጥ የንባብ ጊዜውን አያጠፋም። ይህ ማለት ግን ጨርሶ መዝገበ ቃላት አይጠቀምም ማለት ሳይሆን የሚጠቀመው አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ነው። ብዙውን ጊዜ የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው ሁኔታ በመገመት በትስስር የሚሰጡትን ፍቺ ለአጠቃላይ ጊዜ ያውላል (Ur, 1996) ።

ለውጤታማ ንባብ ተማሪዎች እንዲበረታቱ ማድረግ ያለብን፣ እንግዳ ቃላት ሲያጋጥሟቸው የገቡበትን ዐውድ መሠረት በማድረግ ፍቻቸውን የመገመት ልምድ እንዲያዳብሩ ነው። የትምህርት አቀራረቡም፣ ተማሪውን የቃል በቃል ፍቺ ከመጠይቅ ወይም ከምንባቡ የወጡ ቃላትን በተናጠል ፍቻቸውን ከማስጠናት ታቅቦ፣ የተለያዩ ፍንጮችን በመስጠት አገባባዊ ፍችን የመስጠት ብልሃትን የሚያለማምድ መሆን አለበት (Grellet 1981)። ይህንንም ስልት ተማሪዎች እንዲያዳብሩት ለማድረግ፣ የቃላት ፍች እንዲገምቱ የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራትን ንባቡን ከመጀመራቸው በፊት ማቅረብ ተገቢ ነው (Nattall 1982, Ur, 1996)።

### 2.7.5 ለግል ንባብ ትኩረት መስጠት

ውጤታማ አንባቢ ንባብ በግል የሚከናወን ተግባር መሆኑን ተገንዝቦ ለግሉ የፀጥታ ንባብን ተግባራዊ የማድረግ ልምድና ችሎታ አለው። በግል የፀጥታ ንባብ ማድረግ የንባብ ፍጥነትን ለማሻሻልና ለግንዛቤ ድምፅን ከፍ አድርጎ ከማንበብ የበለጠ ውጤታማ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ (May, 1990)። ስለዚህ የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት ትኩረት ማድረግ ያለበት ተማሪውን የጸጥታ ንባብ በማለማመድ ላይ ነው።

በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚደረገው የንባብ ትምህርት ለምን ዓላማ፣ ምንና እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው የተገነዘቡ ውጤታማ ተማሪዎችን ለማፍራት የሚያግዝ በመሆኑ፣ የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪዎቹ በመምህሩ ወይም በተማሪዎች ከፍ ባለ ድምጽ የሚነበቡ ምንባቦችን እንዲያዳምጡ ከማድረግ ተቆጥቦ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቹ ራሳቸው በጸጥታ የሚያነቡበትን ሁኔታ የሚያመቻች መሆን አለበት (Silbersten, 1994, Nattall 1982)።

### 2.7.6 ንባብን ከተገቢ የማንበብ ስልትና ፍጥነት ጋር ማስማማት

ጥሩ አንባቢ ሁሉንም ዓይነት ጽሑፍ ተመሳሳይ በሆነ ፍጥነትና ስልት አያነብም፤ አንድን ጽሑፍ ከሚያነብበት ዓላማ፣ ከጽሑፍ ይዘት፣ ጽሑፉ ከያዘው መረጃ ስፋትና ጥልቀት አንጻር የንባብ ስልቱንና ፍጥነቱን በማጣጣም ያነባል።

ሁሉንም የጽሑፍ ዓይነት ተመሳሳይ በሆነ ስልትና ፍጥነት ማንበብ፣ የጽሑፉን ሐሳብ ለመገንዘብና ውጤታማ አንባቢ ለመሆን እንደማያስችል ይታመናል (May, 1990)። ስለሆነም ተማሪው ይህንን ተረድቶ ከሚያነብበት ዓላማና ከሚያነበው ጽሑፍ ዓይነት አንጻር የንባብ ስልቱንና ፍጥነቱን በማለዋወጥ የማንበብ ልምዱን እንዲያዳብር ማገዝ ያስፈልጋል፤ ለዚህም ተማሪውን ከተለያዩ የንባብ ስልቶችና ፍጥነት ጋር በማስተዋወቅ ማለማመድ ተገቢ ነው (Nattall 1982, Johansten 1988)።

ንባብ ዓላማን መሰረት ባደረገ መልኩ የሚከናወን ተግባር ነው (Grellet 1981)። ይኸውም፡- ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት፣ ውስን መረጃዎችን ለማግኘት ብቻ፣ አንድ መመሪያ ተከትሎ የሆነ ተግባር ለማከናወን፣ የግል አመለካከትን ለማስማማትና እንዲሁም አጠቃላይ ግንዛቤን ለመጨበጥ ሊነበብ ይችላል። ለነዚህ ሁሉ የንባብ ምክንያቶችም የአነባብ ስልቱ ይለያያል፤ ይህ መሆኑ ደግሞ የአነባብ ፍጥነቱም የተለያየ እንዲሆንም ያስገድዳል (Grellet 1981)።

የንባብ ትምህርት ዓላማ ተማሪውን ከተለያዩ የንበብ ስልቶች ጋር በማስተዋወቅ ጥሩ የንባብ ስልትን እንዲያዳብር ማገዝ ነው (Grellet 1981)። ስለሆነም ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ማንኛውም የቋንቋ መምህር በንባብ ወቅት ጥሩ አንባቢያን የሚጠቀሙባቸውን ስልቶች በመገንዘብ ሊያስተምር ይገባል። ምክንያቱም የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ስልቶችን ማስተማር ተማሪዎች የተለያዩ ዓይነት ጽሑፎችን በትክክል ለመረዳት ያግዛቸዋል ።

## 2.8 የንባብ ስልቶች

የንባብ ስልቶች በአንድ ምንባብ ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችን አእምሮ ውስጥ ለማስገባትና ወደኋላ ላይ ለማስታወስ ይረዱት ዘንድ አንድ ተማሪ የሚጠቀማቸው ተግባራት ናቸው። እነዚህም ስልቶች አጠቃቀማቸው እንደ ምንባቡ ባህሪ፣ እንደ አንባቢው ዓላማና እንደንባብ አውዱ ሊለያይ ይችላል (Wallace, 1993: 57)። ዋና ዋናዎቹንም እንደሚከተለው ባጭሩ ለመግለጽ ተሞክሯል።

### 2.8.1 ትንበያ

ትንበያ አንድ ምንባብ ከመነበቡ በፊት ወይም በመነበብ ላይ እያለ ቀጣይ ሊመጣ የሚችለውን የምንባቡን ይዘት ለመገመት የሚያስችል ስልት ነው። ጥሩ አንባቢዎች

አስቀድመው መላ ለመምታት አነስተኛ ናሙናን በመጠቀም አንድን ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት የትንበያ ስልትን በከፍተኛ ደረጃ ይጠቀማሉ፡፡ ይህንንም ስልት ተማሪዎች የአንድን ምንባብ ርዕስ፣ ዐ.ነገሮች ሰንጠረዦች፣ ካርታዎችና ስዕሎች፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ስነ-ልሳናዊና ኢ-ስነልሳናዊ መረጃዎችን ያላቸውን ቀደምት እውቀት መሰረት በማድረግ መተንበይ እንደሚችሉ ማስተማር ይቻላል፡፡ ይህም ስልት ተማሪዎች የምንባቡን ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲገምቱና ቀደምት ዕውቀታቸውንም ስለሚቀሰቅስ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል (Chia,2001:25)፡፡

### 2.8.2 ማስታወሻ መውሰድ

ይህ ስልት የአንድን ምንባብ ይዘት አጠቃሎ የማቅረብ አካሄድ የተከተለ ስልት ሲሆን በተለይም በእጃቸው የመማሪያ መጽሐፉ ለሌላቸው ተማሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው (Harris and Sipay 1990: 613)፡፡ ይህ ስልት አንባቢዎች መረጃዎች የሚወጡባቸውንና ተጽፈው የሚቀመጡባቸውን የተለያዩ ጽሑፎችን ለመመልከት ጠቃሚ የሆነ ስልት በመሆኑ ተማሪዎች ሊማሩት ይገባል፡፡ ይህም መረጣና ማሰብ ላይ የተመሰረተ ንባብ ለማከናወን ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም ዝርዝርና አላስፈላጊ ሃሳቦችን የመለየትና በሀሳቦች መካከል ያሉትን ዝምድናዎች ማጤንን የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡

### 2.8.3 ድጋሚ ንባብ

ይህ ስልት የማካካስ ሚናን የሚጫወት የንባብ ስልት ነው (Mei-yun, 1996:181) ፡፡ ይህ ስልት ምንባብ በሚነበብበት ጊዜ ኢ-ተረድኦትን ለማስወገድና አንባቢው ይዞት የመጣውን ለማረጋገጥ ሲባል የሚከናወን ነው፡፡ ስለዚህ አንብቦ መረዳትን ለማቀላጠፍ ተማሪዎች ይህንን ስልት ሊማሩ ይገባል፡፡

### 2.8.4 ማጠቃለያ

ማጠቃለል አንባቢዎች ከምንባቡ እንዲማሩና የምንባቡን ይዘት እንዲያስታውሱት የሚረዳ ስልት ነው፡፡ ማጠቃለል የአንድን ምንባብ አስቸጋሪ ቃላትንም ለመቋቋም ያስችላል (Gillan,1993:91)፡፡ ማጠቃለል የቀረበውን ምንባብ የሚወክል አጭርና አጠቃላይ ጽሑፍ ነው፡፡ ማጠቃለል የሚጠቃለለውን ጽሑፍ መረዳትን መገምገምን

የማሳጠርና የማሻሻል ችሎታን የሚጠይቅ ተግባር ነው። ይህ ተግባሩም ቀላል ባለመሆኑ ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ ለማሳጠር ከሚያግዙት ዘዴዎች ጋር ሊተዋወቁ ይገባል።

#### 2.8.5 ቅኝት

ይህ ስልት ኢቴክስታዊ መሳሪያዎችን በመጠቀም የምንባቡን ይዘትና ቅንብር በፍጥነትና በብቃት ለመቃኘት የሚያስችል ነው (Hyland,1995:107)። ቅኝት የሚነበበውን ጽሑፍ ዋና ዋና ክፍሎችን አስቀድሞ ማሰስ ማለት ነው። ይኸውም የአንቀፆች የመጀመሪያና የመጨረሻ ዓረፍተነገሮች፣ መግቢያ፣ ማጠቃለያ፣ ወዘተ. መመልከትን ይጠይቃል። እነዚህን ክፍሎች ማየት ለዋናው ንባብ የሚጠቅሙ መነሻና መሰረታዊ ግንዛቤዎችን ያስጨብጣል።

ባጠቃላይ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማዳበር ውጤታማ አንባቢ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ የንባብ ዓይነቶችን መጠቀም ተገቢ እንደሆነ የሚታመን ሲሆን መምህራንም ተማሪዎች ምን ዓይነት ስልቶች እንደሚያስፈልጓቸው ለምን እንደሚያስፈልጓቸው መቼ ማስተማር እንዳለባቸው ሊገነዘቡ ይገባል ።

## 2.9 የንባብ ክሂሎች

አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ውጤታማ አንባቢ እንዲሆኑ ለማስቻል ተማሪዎችን ከተለያዩ የንባብ ስልቶች ጋር ማስተዋወቅ ተገቢ እንደሆነ ሁሉ፣ የንባብ ክሂሎችንም እንዲማሩ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን Gebhard, (1999:200) ይገልፃሉ። ዋና ዋናዎቹን እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፤

#### 2.9.1 የትኩረት ንባብ (Detailed reading)

እያንዳንዷን ጥቃቅንና ዝርዝር መረጃ በትኩረት በመመርመር ውስብስብ መረጃዎችን ለመገንዘብ የሚደረግ ንባብ ነው። ይህ ክሂል በዝግታ የማንበብ ፍጥነትን የሚሻ ሲሆን ከ125 ቃላት ባልበለጠ ፍጥነት የሚነበብ ነው። የትኩረት ንባብ፣ የሳይንስ ሙከራዎችን ለማካሄድ፣ እውነታን ከግል አስተያየት ለመለየት፣ በቻርትና በስዕላዊ መግለጫዎች የቀረቡ መረጃዎችን አጠቃሎ ለመገንዘብ የግል አመለካከትን ከቀረበው ጽሑፍ ጋር ለማነጻጸርና ለመገምገም ለሚደረጉ የንባብ ተግባራት የሚውል ነው። ተማሪዎች በየዕለቱ

በሳይንስ የትምህርት መስክ የሚቀርቡ ጽሑፎችና የማስተማሪያ መሣሪያዎች የሚይዙትን እጅግ የታመቁ መረጃዎችን ለመረዳትና የተለያዩ ሙከራዎችን ለማካሄድ በጥንቃቄና በዝግታ ፍጥነት የማንበብ ተግባር ስለሚያጋጥማቸው፣ የትኩረት ንባብን ለማዳበር የሚያግዙ መልመጃዎችን በመጠቀም ማለማመድ ይገባል። መልመጃዎቹም እውነታን የመለየት፣ በዋናና በዝርዝር ሐሳቦች መካከል ያለ አንድነትን ማመልከት፣ ለተወሰኑ ጽንሰ ሃሳብ ጥያቄዎች መልስ የመስጠት፣ መመሪያን ተከትሎ ተግባር የመፈጸም ሊሆኑ ይችላሉ (Nattall,1981:34)።

### 2.9.2 የአሰሳ ንባብ (Scanning)

ውስን የሆኑ መረጃዎችን ብቻ ለማግኘት በፍጥነት የሚደረግ ንባብ ነው። እንደ ዓመተ-ምህርት፣ የሀገርና የሰው ስሞች፣ አሃዛዊ መግለጫዎች በፍጥነት በመቃኘት የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት የሚደረግ ንባብ ነው። በአሰሳ ንባብ ትኩረት የሚሰጠው ለሚፈለገው መረጃ ብቻ ስለሆነ አላስፈላጊ ዝርዝር ጉዳዮችን በፍጥነት ማለፍን ይጠይቃል (Nattall,1981:34)። ስለዚህ ተማሪዎችን የአሰሳ ንባብ ለማለማመድ ብዙ መረጃዎችን ለማስታወስ ሳይጨነቁ የተፈለጉ መረጃዎችን ብቻ እንዲፈልጉ ከንባብ በፊት ቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፤ ለምሳሌ ብያኔ፣ የሀገር ወይም የሰው ስምን፣ የኬሚካል ስሞች፣ የአየር ንብረት መጠንን ለይተው እንዲያመለክቱ የሚጠይቁ ክንዋኔዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

### 2.9.3 የእይታ ንባብ (Skimming)

የምንባቡን አጠቃላይ ሐሳብ ለማግኘት በፍጥነት የሚደረግ ንባብ ነው። ፍጥነቱም ከአሰሳ ንባብ ፍጥነት ባነሰ መልኩ የሚከወን ሲሆን፣ ምንባቡን ፈጠን ባለ መልኩ መመልከትን ይሻል። ይህን ክሂል ለማለማመድ የሚቀርቡ ክንዋኔዎች የሚፈጸሙበትን የጊዜ ገደብ ወስኖ ለተማሪው መግለጽ እንደሚገባና በግልና በጸጥታ ንባብ የሚከወን መሆኑን መምህራን መገንዘብ እንዳለባቸው (Nattall,1981:34) ያሳስባሉ።

### 2.9.4 ዐውዳዊ ንባብ (Inferring)

ይህ ክሂል በቀረበው ምንባብ ውስጥ የተካተቱትን ጽንሰ ሐሳቦች የያዙ ቃላትና ሀረጎች ከተዋቀሩበት አንጻር፣ አገባባዊ፣ ሙያዊ፣ ባህላዊና ተጠየቃዊ ፍንጮችን በመጠቀም

በትስስር የሚያገኙትን መልእክት ለመገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ ይህንንም ክሂል ተማሪዎች እንዲያዳብሩት ለማድረግ ከዐውዳዊ አገባባቸው አንጻር የቃላትን ፍቺ ለመገመት የሚያስችሉ መልመጃዎችን በማቅረብ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

### 2.9.5 ሰፊ ንባብ

ይህ የንባብ ክሂል በተማሪ ምርጫ ላይ የተመሰረተና ረጅም ልቦለድ፣ አጭር ልቦለድ፣ ተውኔት፣ ግጥሞች፣ ወዘተ. የመሳሰሉ ረጃጅም ጽሑፎችን ማንበብን የሚጠይቅ ነው፡፡ ሰፊ ንባብ አንባቢው ራሱ በመረጠው መንገድና የግሉን ችሎታ በመጠቀም ይከናወናል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መምህራን ሚና ተማሪዎች ሊረዱት የሚችሉትን ጽሑፍ ራሳቸው እንዲመርጡ መንገድ ማሳየትና ምርጫቸው እንዲጠበቅላቸው መፍቀድ ይሆናል (Gebhard,1999:208)፡፡ ይሁን እንጂ ግን መምህራን የመረጡትን ረጅም ጽሑፍ እንዲያነቡ በመፍቀዱ ላይ ብቻ መወሰን የለባቸውም፡፡ ማለትም ተማሪዎች አንድን ረጅም ጽሑፍ ምን ያህል እንዳነበቡትና እንደተከታተሉት የሚቆጣጠሩበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡ አንድ መምህር አንብቦ መረዳትን ለመከታተል መጠቀም ከሚገባቸው የመከታተያ ስልቶች መካከል አንዱ የንባብ ዘገባ ነው፡፡ ይህ መከታተያ በመምህራን አማካይነት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችልና አንድ ጽሑፍ በተማሪዎች ከተነበበ በኋላ ንባቡን መሰረት በማድረግ የሚቀርብ ዘገባ ነው (አለም፣ 1992፣107)፡፡ በመጠየቅ ስልት ስለ ጽሑፍ ጭብጥ፣ዓይነት፣ የደራሲ ማንነት፣ ወዘተ. እንዲጠያየቁ በማድረግ መከታተል ይቻላል፡፡

### 2.9.6 ሂሳዊ ንባብ

ንባብ ማንኛውም በጽሑፍ የቀረበ ነገር ተጠቅሞ መረጃን/ መልዕክትን መቀበያ ሂደት ብቻ እንዲሆን ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም፡፡ ምክንያቱም የአንባቢው አስተያየት ወይም ግምገማ ሊከታተልበት ስለሚችል፡፡ ይህንንም ለማድረግ፣ ማለትም ማንኛውም አንባቢ የሚያነበውን ጽሑፍ ለመገምገም ሂሳዊ ንባብን የግድ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በዚህም ወቅት ምንባቡን ለመገምገም ዓላማ ሲባል የአንባቢውን በጥልቅ ማሰብ ይጠይቃል፡፡ ዓላማውም ደራሲው ምን?ለምንና? ለማን? እንደፃፈ ለመገምገም ነው (Mei-Yun, 1995:186)፡፡ በዚህም መሰረት ተማሪው የሂሳዊ ንባብ ችሎታውን እንዲያዳብር ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም መምህሩ ተገቢ የሆኑ ተግባራትን

በማዘጋጀትና በመጠቀም ተማሪዎች የሂሳዊ ንባብ ችሎታን እንዲያዳብሩ የማድረግ ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሚጋጩ መረጃዎችን ያዘሉ ምንባቦች ሲያነቡ ስለሚማርኩ፣ የተለያዩ መረጃ የያዙ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ምንጮች ለሂሳዊ ንባብ ተስማሚ እንደሆኑ መገመት አያዳግትም፡፡ ለተማሪዎች ቀደምት ዕውቀትና እምነት አዲስ የሆኑ ሐሳቦችንና መረጃዎች የሚካተቱባቸው ጽሑፎችም ተገቢ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ባጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ንዑስ ክሂሎች ምንም እንኳ የተለያየ ባሕርይና ዓላማ ያላቸው ቢሆኑም ተለያይተው የሚታዩ ግን አይደሉም ይህ ማለት አንዱ ሲተገበር ሌላውም አብሮ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ሰፊ ንባብ ስናደርግ ሂስ እየሰጠን ሊሆን ይችላል፡፡ (Nunan1995:33, Harris and Sipay, 1990:586)

## 2.10. የቀደምት ሥራዎች ቅኝት

የንባብ ትምህርት ወቅታዊና ውጤታማ እንዲሆን በማድረጉ ረገድ በተለያዩ ጊዜያት የሚካሄዱት ጥናቶች ጥቆማ የጎላ ሚና ሊኖረው እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ በሀገራችንም በአሁኑ ወቅት የንባብ ትምህርት ከዘመናዊ ትወራና ትግበራ አንጻርም ምን ይዘት እንዳለው በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሁለተኛ ዲግሪ፣ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያና ለሌሎች ዓላማዎች በዘርፉ ጥናቶች በመካሄድ ላይ ናቸው፡፡ ከዚህም በመቀጠል ከዚህ ጥናት ርዕስ ጋር ዝምድና ያላቸው ስራዎች ይቃኛሉ፡፡

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ከተሰሩ ጥናቶች አንዱ የሆነው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማርኛን በማስተማር መርሃ-ግብር በ1992 ዓ.ም በእንግዳ "ቶፕ ዳውን (Top-Down) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት" የሚለው ሲሆን ይህም ፍትነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም የቶፕ ዳውን የንባብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማዳበሪያ ዘዴ እስራ ላይ ቢውል የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ሌላው ደግሞ በ1990 ዓ.ም በየኔሰው "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ" በሚል

ርዕስ የተሰራው ሲሆን ይህም ጥናት የተከተለው ዘዴ ከላይ ከተጠቀሰው ጥናት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፡ "ከተራክቧዊ የንባብ ክሂል አንጻር የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍ አንብቦ መረዳትን በተመለከተ ለሚዘጋጁ፣ አንብቦ መረዳትን ለሚያስተምሩ፣ እንዲሁም ከዚያም አልፎ በሌሎች ቋንቋዎችና አንብቦ የመረዳትን ክሂል በተመለከተ የማስተማሪያ መሳሪያ የሚያዘጋጁና የሚያስተምሩ ሞዴሉን ከተጠቀሙ፣(ሀ) ስነልሳን በማስተማር፣(ለ) የንባብ ፍጥነትን በማሻሻል፣ (ሐ) የጽሑፉን መልዕክት በትክክል በመረዳትና (መ) አዲስ ዕውቀትን ቀደም ሲል ከነበረው እውቀት ጋር በማያያዝ በኩል ሞዴሉ ጠቀሜታ እንደሚኖረው በውጤቱ ላይ ገልጸዋል፡፡ ከላይ የቀረቡት ሁለቱ ጥናቶች በንባብ ትምህርት ላይ ማተኮራቸው ከዚህ ስራ ጋር የሚያመሳስላቸው ሲሆን በዓላማ፣ በክፍል ደረጃ፣ በተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያና በተካሄዱበት ጊዜ ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያሉ፡፡

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ከሌሎች ጥናቶች በተሻለ መልኩ ተመሳሳይነት ያለው በ1996 በተክሉ "በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ዘጠነኛ ክፍልን በሚያስተምሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የንባብ ትምህርት ትግበራ ግምገማ ላይ ያተኮረ ጥናት" ሲሆን ይህም ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም "በሁለቱም አውዶች የሚሰጡት የአንብቦ መረዳት ትምህርቶች አቀራረቦችና ዘዴዎች ልዩነት እንደማይታይባቸውና ከጥንታዊ አቀራረብና ዘዴዎች ያልተላቀቁ እንደሆኑ በውጤቱ ይፋ አድርጓል፡፡

ይህ በ1996 ዓ.ም የተካሄደው ጥናት በሁለት ትምህርት ቤቶች የንባብ ትምህርት አቀራረብ አንድነትና ልዩነት ላይ የሚያተኩር መሆኑ፣ እንዲሁም በተካሄደበት ጊዜ፣ ቦታና የክፍል ደረጃ ከዚህ ጥናት ጋር የማይመሳሰል ሲሆን ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን የተጠቀመና ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ መሆኑ ከአሁኑ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ገላጭ የምርምር ዘዴ ስሙ እንደሚያመለክተው ተመራማሪው አንድ ጉዳይ አንስቶ የነበረው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በትረካዊ መንገድ የሚያቀርብበት ነው፡፡ ያለው እንዳወቀ (1988)፡፡ በዚህም ጥናት ውስጥ የተነሳውን ጉዳይ በተመለከተ የተሰበሰቡት መረጃዎች የቀረቡት ትረካዊ በሆነ መንገድ ስለሆነ የጥናቱ ዘዴ በዋናነት ገላጭ ምርምር ዘዴ ላይ እንዲመሰረት ሆኗል፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

ይህን ጥናት ለማካሄድ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን፣ መረጃዎችም በዋናነት የተሰበሰቡት ከተመረጡ ሶስት ትምህርትቤቶች ውስጥ በተተኳሪው የክፍል ደረጃ አማርኛ ቋንቋን ከሚያስተምሩ መምህራንና ተማሪዎች ነው፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በናሙናነት በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ መረጃዎችንም ለመሰብሰብ በጥቅል ንሞና ዘዴ ላይ በመመስረት መምህራን የተመረጡ ሲሆን፣ ተማሪዎችን ለመምረጥ ደግሞ የነሲብ ንሞና ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

- የትምህርት ቤት አመራረጥ

በቡለን ወረዳ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሶስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡበት ዘዴ የነሲብ ንሞና ሲሆን የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ቡለን አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል፣ ኤጋንቦና ኤቆንጤ 1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክልና ባሩዳ 1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ በቡለን ወረዳ ስር የሚገኙትን አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶችን በሙሉ በጥናቱ ውስጥ እንደመረጃ ምንጭነት

ለማካተት ከትምህርት ቤቱ ቁጥር አንጻር መረጃ ለመተንተን ሰፊ ጊዜ የሚጠየቅ እና አድካሚ በመሆኑ ከላይ የተገለጹት ሶስት ትምህርት ቤቶች እንዲመረጡ ተደርጓል።

❖ የመምህራን አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ እንዲካተቱ የተደረጉት፣ በኤጋንቦና ኤቆንጤ፣ በቡለንና ባሩዳ አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች 8ተኛ ክፍልን አማርኛ የሚያስተምሩ መምህራን ሲሆኑ፣ በዚህ የክፍል ደረጃ በማስተማር ላይ የሚገኙ ስድስት መምህራን በሙሉ በመረጃ ምንጭነት ተመርጠዋል።

❖ የተማሪዎች አመራረጥ

ለጥናቱ በናሙናነት ከተመረጡት ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉሳይክል ትምህርት ቤቶች ከሚገኙ የ8ተኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ ለጥናቱ እንደ አጋዥ የመረጃ ምንጭነት እንዲያገለግሉ በጥቅል ንሞና ዘዴ ክፍሎች ከተወሰዱ በኋላ ከአንዱ ትምህርት ቤት ሃያ ስምንት፣ ከተቀሩት ትምህርት ቤቶች ከእያንዳንዱ ሃያ ስድስት ባጠቃላይ ሰማንያ ተማሪዎች መረጃ እንዲሰጡ በነሲብ ንሞና ዘዴ ተመርጠው በናሙናት እንዲካተቱ ተደርገዋል።

## 3.4 የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሶስት ናቸው። መረጃዎችንም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅና በቡድን ቃለመጠይቅ አማካይነት ለመሰብሰብ ተሞክሯል። ምንም እንኳ ጥናቱ በዋነኝነት መሰረት ያደረገው የመምህራንን የንባብ ትምህርት ክፍል ውስጥ ትግበራን ቢሆንም ንባብን ለማስተማር እንደዋነኛ መሳሪያ መምህራን ሲገለገሉበት ይታይ የነበረው የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፉን ስለነበር በጣም አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቅኝት ተደርጎበታል።

### 3.4.1 ምልከታ

የምልከታ ዘዴ መረጃ ሰብሳቢው ሰው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልግባቸው ተጠኚዎች ጋር ወይም አካባቢ በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ እንዴ እንደሚሰሩ፣ ምን እንደሚናገሩ ወዘተ እራሱን በሚመቸው፣ አስተማማኝና ትክክለኛ መረጃ በሚያስገኝለት መንገድ መረጃ የሚሰበስብበት መንገድ ነው Sadhu,

and Amarjit (1980)። ከዚህም ይህን ጥናት ለማካሄድም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳትን ትምርት አተገባበር፣ የተማሪዎች ተሳትፎና አጠቃላይ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ድባብ ምን እንደሚመስል ለመለየት የሚያስችሉ አስተማማኝና ትክክለኛ መረጃዎችን መሰብሰቡ ተገቢ ነው። ለዚህም የምልከታ መከታተያ ዝርዝር ቅጽ ስርዓት ባለው መንገድ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ የመከታተያ ቅድም ምዕራፍ ሁለት ላይ ያለውን ክለሳ ድርሳንና የአጥኚው የስራ ልምድ እንዲሁም አጥኚው በክፍል ውስጥ ሊተገበሩ ይችላሉ ብሎ ያሰባቸውን ባህሪያት አሟልቶ እንዲይዝ ተደርጓል። በዚህ የምልከታ መከታተያ ዝርዝር ውስጥ፡- በንባብ ትምህርት ደረጃዎች ትግበራ፣ በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ባህሪና በአንብቦ መረዳት ትምህርት ሂደት የመምህራን ሚናና ግንዛቤ የሚሉት ጉዳዮችን በተመለከተ በ12 የአንብቦ መረዳት ትምህርቶች ላይ በጥልቀት ምልከታዎች ተካሂደዋል።

### 3.4.2 የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቅ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዜዴዎች ጋር ሲነጻጸር ጊዜን፣ ጉልበትንና ገንዘብን ይቆጥባል። ይህም ሲባል ተመራማሪው መጠይቁን ካዘጋጀ በኋላ መረጃውን ለመሰብሰብ ከእያንዳንዱ ተጠኚ ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ አይወያይም፤ ማብራሪያ በመስጠት ጊዜ አያጠፋም። ከዚህም ሌላ የመላሾቹን ማንነት ስለማይገልጽ መላሾቹ አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ሊያበረታታቸው ይችላል። ያለው እንዳወቅ (1998)። ከዚህም በመነሳት አስተማማኝ መረጃዎችን ለማግኘት ሲባልና እንዲሁም የቀረቡት ጥያቄዎች በርካታ ስለሆኑ ጊዜን ለመቆጠብ ብሎም አሰልቺነትን ለመቀነስ ታስቦ የጽሑፍ መጠይቁ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል።

የጽሑፍ መጠይቁ ተተኳሪ በሆኑት ሦስት 1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስለሚገኙ ተጠኚ መምህራን አጠቃላይ መረጃ፣ ስለአንብቦ መረዳት ትምህርት ያላቸውን ግንዛቤና የክፍል ውስጥ ትግበራን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታልሞ የተዘጋጀ ሲሆን ተግባር ላይ እንዲውል ተደርጓል። ይህ መጠይቅ ስለተጠኚ መምህራን አጠቃላይ መረጃን ስለአንብቦ መረዳት ያላቸውን ግንዛቤና አቀራረባቸውን አስመልክቶ መረጃ የሚሰጡ ዝግና ክፍት ጥያቄዎችን ያካተተ ነው። የጽሑፍ መጠይቁም በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ስድስት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሞሉት የተበተነ ሲሆን መጠይቆቹ

በሙሉ ተሞልተው ተመልሰዋል። መምህራኑም በርጋታ በማንበብ ተገቢ መረጃ ይሰጡ ዘንድ በቂ ጊዜም ተሰጥቷቸዋል። በጽሑፍ መጠይቅ ውስጥ የሚገኙት መጠይቆች በትንተናው ጊዜ በሠንጠረዥ መልክ ቀርበዋል።

በሠንጠረዥ ውስጥ የሚገኙትም አሃዞች የየራሳቸው ውክልና አላቸው። እነዚህም ግንዛቤን በተመለከተ 5 በጣም እስማማለሁ 4 እስማማለሁ 3 መወሰን ያስቸግረኛል 2 አልስማማም 1በጣም አልስማማም የሚሉ ሲሆን ትግበራን በተመለከተ ደግሞ 4 ሁል ጊዜ 3 አብዛኛውን ጊዜ 2 አንዳንድ ጊዜ 1 ፈጽሞ የሚለውን ሃሳብ ያመለክታሉ።

### 3.4.3 የቡድን ቃለ መጠይቅ

የቡድን ቃለ መጠይቅ በሚካሄድበት ወቅት እንደሁኔታው ሊለዋወጥ፣ እንደመላሹ አይነት ሊሻሻል፣ እንደጠያቂው ችሎታ ሊቀያየር ይችላል። ይህም ከጽሑፍ መጠይቅ በተሻለ መልኩ ለመላሹ ጥያቄዎችን ለማብራራት፣ ግልጽ ያልሆኑ ምላሾችን ይበልጥ ግልጽ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ መላሹ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይሄድና የተፈለገውን መረጃ እንዲሰጥ ለማድረግ ስለሚያስችል ጠንካራ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ይሰኛል (Best 1981)። ስለዚህ ተማሪዎቹ 8[ተኛ] ክፍል ከመሆናቸውም በተጨማሪ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ የጽሑፍ መጠይቅ ቢቀርብላቸው የቀረበውን ሐሳብ ተረድተው አስተማማኝ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ወይ? የሚለው አጠራጣሪ ሲሆን እንደሚችል መገመቱ አያዳግትም። ስለሆነም በግንባር በመገኘት ያልገባቸውን እንዲጠይቁ በመፍቀድና አስፈላጊውን ማብራሪያ በመስጠት መረጃዎችን መሰብሰቡ የተሻለው መንገድ ሆኖ ስለተገኘ የቡድን ቃለመጠይቁ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ይኸውም የክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ተጨማሪ አጋዥ መረጃዎችን ለማከልም ከተማሪዎች ጋር የቡድን ቃለ መጠይቆች ተካሂደዋል። ተተኳሪ የነበሩት ሶስት ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ ከአንዱ ትምህርት ቤት ሃያ ስምንት ተማሪዎች የተመረጡ ሲሆን ከቀሩት ሁለት ትምህርት ቤቶች ደግሞ ከእያንዳንዱ ሃያ ስድስት በአጠቃላይ ሰማንያ ተማሪዎች ተመርጠው ወደ አነስተኛ ቡድን (6 አባላት) ከተከፈሉ በኋላ ቢያንስ በአማካይ በአንድ ጊዜ ሃምሳ ደቂቃዎችን የፈጀ፣ የቡድን ቃለመጠይቆች ተደርገዋል። የተገኙት መረጃዎችም ስርዓት ባለው መልኩ ተደራጅተው በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል።

## 3.5 የጥናቱ ክንውን

በቡለን ወረዳ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ላይ ሲሆን ጥናቱ በ2003 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በአንደኛው መንፈቀ-ዓመት ላይ የተመሰረተ ነው።

ለዚህ ጥናት ፣ የሚያስፈልጉ በቂና ተገቢ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ በነሲብ ንሞና አማካይነት የተለያዩ ትምህርት ቤቶችን መምረጥ ተቀዳሚ ስራ ነበር። ጥናቱ ትኩረት ባደረገው የክፍል ደረጃ አማርኛ ቋንቋን ከሚያስተምሩ መምህራን በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት የሚፈለገውን መረጃ ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ ከትምህርት ክፍሉ መሪዎች ጋር መገናኘትና የዓመቱን ትምህርት እቅዶች መከታተል አስፈላጊ ነበር። የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ ትግበራን በተመለከተ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በትምህርቱ ሂደት የመምህራንና የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ባህሪያት ለመከታተል የሚያስችል የምልከታ መከታተያ ዝርዝር ማዘጋጀት ተከታዩ ስራ ነበር። የምልከታ መከታተያ ዝርዝሩ በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ላይ ተተግብሮ በጥናቱ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል። ከዚህ በመቀጠል የተሰራው ስራ በመምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ ዝግጅት ነበር። የጽሑፍ መጠይቅም በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተተኳሪ በሆነው የክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲሞላ ተደርጓል። የተሰበሰበውም መረጃ ለመደበኛው ጥናት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል። በመቀጠልም በሦስቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተተከኳሪው የክፍል ደረጃ ከሚገኙ ተማሪዎች በቡድን ቃለመጠይቅ መረጃዎች ለመሰብሰብ ተሞክሯል። በመጨረሻም የንባብ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ በሶስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ስርአት ባለው መልኩ ተደራጅተው ሊተነተኑ ችለዋል።

## 3.6 የመረጃዎች አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት በዋናነት የ8ኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብን መፈተሽ ላይ የተመሰረተ ሲሆን። ይህንንም ፍተሻ ለማካሄድ ተስማሚ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተግባር ላይ ውለዋል። በዚህም መሰረት በምልከታና በቡድን ቃለመጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም

ተተንተነዋል፡፡ በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች ደግሞ አሀዛዊ መተንተኛ ዘዴን በመጠቀም ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

**በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች**

2. ቡለን አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት
3. ኤጋንቦና ኤቆንጤ አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት
4. ባሩዳ አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት

ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች አቀራረብና ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ሥር ስለ አንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር በምልከታ፣ በጽሑፍና በቃለመጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ይተነተናሉ፤

### 4.1 የተጠኚ መምህራን ዳራ

ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት እንዲያገለግሉ ከሦስቱም ትምህርት ቤቶች የተመረጡት ስድስት መምህራን በተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ሁሉም ዲፕሎማዎች ናቸው። የአገልግሎት ዘመናቸውን በተመለከተ ሶስቱ መምህራን አራት ዓመት ያገለገሉ ሲሆን፣ የተቀሩት ሶስቱ ደግሞ የሁለት ዓመት የማስተማር ልምድ እንዳላቸው የተገኘው መረጃ ያመለክታል። መምህራኑ ቋንቋ በሚል ጥቅል መጠሪያ አማርኛንና እንግሊዝኛን አንድ ላይ በመውሰድ የሰለጠኑ ሲሆን በዩኒቨርስቲ/ኮሌጅ ቆይታቸውም ሆነ በተገኙበት የስራ ገበታ ላይ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚያስችል የተለየ ስልጠና እንዳልወሰዱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ከዚህም መረዳት የሚቻለው መምህራኑ የረጅም ጊዜ የስራ ልምድ እንደሌላቸው፣ አማርኛ ቋንቋን በአብይነት እንዳልሰለጠኑና በኮሌጅ ቆይታቸውም ሆነ በስራ ገበታ ላይ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚያስችል የተለየ ስልጠና እንዳልተሰጣቸው ነው። ይህም ሁኔታ አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ረገድ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ይሁን እንጂ አንድ የቋንቋ መምህር ስለአንብቦ መረዳት ትምህርት የተለየ ሥልጠና አለመውሰዱ በማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል የሚታመን ቢሆንም ግን መምህሩ አንብቦ መረዳትን አስመልክተው በተለያዩ ምሁራን ተዘጋጁ ስራዎችን በማንበብና በመስኩ ከሰለጠኑ ሌሎች የሙያ አጋሮቹ ጋር በመወያየት፣ እንዲሁም ከማስተማር ልምዱ በመነሳትና ራሱን ከዘመናዊ አሰራሮች ጋር በማዋሃድ ግንዛቤውን ለማሳደግ በግሉ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። ከዚህም አንፃር ስለአንብቦ መረዳት ትምህርት ያላቸውን ግንዛቤ ለመፈተሽ የተዘጋጁ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው የሰጥዋቸው ምላሾች እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

ሠንጠረዥ 1፡- ስለ ምንባቦች አቀራረብ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | በአንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ምንባቦች በግልና በዝምታ መነበብ አለባቸው። | - | 2 | | 3 | 1 |
| 8 | በአንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ምንባቦች በመምህራን መነበብ አለባቸው። | - | 2 | 1 | 3 | - |
| 7 | በአንደኛ ደረጃ ሙሉሳይክል ትምህርት አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ምንባቦች በተማሪዎች ተራ በተራ በጮክታ ሊነበቡ ይገባል። | - | 4 | 1 | - | 1 |

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚሳየው፣ በተራ ቁጥር አንድ ላይ ለቀረበላቸው ማለትም ምንባቦች በግልና በዝምታ መነበብ አለባቸው በሚለው ሐሳብ ላይ ሁለቱ መምህራን የተስማሙ ሲሆን አራቱ ግን እንደማይስማሙ ገልጸዋል። ከዚህም ሌላ ምንባቦች በመምህራን መቅረብ አለባቸው በመሚለው ሐሳብ ላይ ሁለቱ መምህራን የተስማሙ ሲሆን ሦስቱ ግን አልተስማሙም እንዲሁም አንዱ መወሰን አልቻልም የሚል ምላሽ ሰጥቷል። በተመሳሳይ ሁኔታም በሦስተኛ ደረጃ ማለትም፣ ምንባቦች በተማሪዎች ተራ በተራ በጮክታ ሊነበቡ ይገባል ተብሎ የቀረበውን ሃሳብ በተመለከተ አራቱ መምህራን እንደሚስማሙ ሲገልጹ አንዱ ለመወሰን እንደተቸገረና የቀረው አንዱ ደግሞ እንደማይስማማ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።ስለ አንብቦ መረዳት ትምህርት መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ የቀረበው ትንተና እንደሚያመለክተው የአብዛኞቹ መምህራን ግንዛቤ የሚያደላው ምንባቦች በተማሪዎች ተራ በተራ በጮክታ መነበብ አለባቸው ወደሚለው ነው። ይህም ሁኔታከተማሪዎች በተገኘው መረጃና በተደረጉት ምልከታዎች ተግባራዊ ሲደረግ ለማስተዋል ተችሏል። ምንም እንኳ ምንባቦች በተማሪዎች ተራ በተራ በጮክታ መነበባቸው ለአንባቢው ተማሪ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚታመን ቢሆንም፣ የዚህ አይነቱ አቀራረብ ግን ከአንብቦ መረዳት ይልቅ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረው መረዳት ይቻላል። ባጠቃላይ መምህራኖች ምንባቦች በተማሪዎች ተራ በተራ በጮክታ እንዲቀርቡ ማድረጋቸው ምንባብ በማንና እንዴት መቅረብ እንዳለበት፣ እንዲሁም የግልና የዝምታ ንባብ ተገቢ አቀራረብ ስለመሆኑ ካለመገንዘባቸው የተነሳ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል።

በአንብቦ መረዳት ትምህርት ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራኑ ለእያንዳንዱ የምንባቡ ክፍል ከፍተኛ ትኩረት እንደማይገባ Ur (1996:148) ያስረዳሉ። ከዚህም አንፃር የመምህራን በምንባብ ክፍሎች ትኩረት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

ሠንጠረዥ 2፡- መምህራን በንዑሳን የምንባብ አተገባበር ትምህርት ላይ ያላቸው ግንዛቤ

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ተማሪዎች በንባብጊዜ የሚያጋጥሟቸውን ከባድ ቃላት በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ሊመዘግቡ ይገባል። | - | 2 | - | 3 | 1 |
| 2 | የአንድ ምንባብ መልዕክት ለመረዳት ተማሪዎች የእያንዳን ዱን ቃል ፍች ማወቅ ይኖርባቸዋል። | - | 4 | 1 | 1 | - |
| 1 | የአንድን ምንባብ መልዕክት ለመረዳት ተማሪዎች የቁልፍ ቃላትን ፍቺ ማወቅ ይኖርባቸዋል። | - | 4 | - | 2 | - |

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው፣ ተማሪዎች በምንባብ ጊዜ የሚያጋጥሟቸውን ከባድ ቃላት መመዝገብ ይኖርባቸዋል በሚለው ሐሳብ ላይ ሁለቱ መምህራን ስምምነታቸውን ሲገልጹ፣ ሶስቱ እንደማይስማሙ መልሰዋል።አንዱ ደግሞ ፈፅሞ እንደማይስማማገልጿል። ከዚህም በመቀጠል የአንድን ምንባብ መልእክት ለመረዳት ተማሪዎች የእያንዳንዱን ቃል ፍች ማወቅ ይኖርባቸዋል በሚል በተራ ቁጥር ሁለት ላይ ለቀረበው ሀሳብ አራቱ መምህራን ስምምነታቸውን ሲገልጹ፣ አንዱ ለመወሰን እንደሚቸገርና የቀረው አንዱ ደግሞ እንደማይስማማ ምላሹን ሰጥቷል። አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ መምህራኑ ተጠይቀው የአንድን ምንባብ መልዕክት ለመረዳት ተማሪዎች የቁል ቃላት ፍቺን ማወቅ ይኖርባቸዋል። በሚለው ላይ፣ አራቱ ሲስማሙ፣ ሁለቱ ደግሞ። እንደማይስማሙ ገልጸዋል። ከዚህም በመነሳት፣ በአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ በምንባብ ክፍሎች ትኩረት ላይ የመምህራኑ ግንዛቤ በጥንታዊ አቀራረብ ላይ የተመሠረተ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

## 4.2 ንባብን በማስተማር ሂደት የመምህራን ሚና

አንድ የቋንቋ መምህር አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ሂደት የሚኖረው ሚና ምቹ የሆነ የክፍል ውስጥ የመማር - ማስተማር ድባብ ማመቻቸት፣ተገቢ የሆኑ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ማቅረብና ሲሰሩም አመራር መስጠት ብሎም ሂደቶችን ከመቆጣጠርና ከማሳየት ያለፈ መሆን የለበትም። ከዚህ በመነሳት አንብቦ መረዳትን በማስተማር ረገድ

የመምህራኑ ሚና ምን ይመስል እንደነበር ለመለየት ምልከታዎች ተካሂደው የነበር ሲሆን፤ ምልከታ ከተደረገባቸው አስራ ሁለት የአንብቦ መረዳት ትምህርቶች መካከል በአስሩ የምንባቡን ይዘት በተመለከተ በመምህራኑ ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን በሁለቱ የአንብቦ መረዳት ትምህርቶች ግን ምንም ዓይነት ማብራሪያ እንዳልተሰጠ ለማስተዋል ተችሏል፡፡ የትምህርቱን ሂደት ከመምራትና ከማሳየት አንጻር በአራቱ ትምህርቶች የመምህራኑ ሚና በመጠኑም ቢሆን የትምህርቱን ሂደት በመምራት ላይ የተመሰረተ እንደነበረ ለማስተዋል የተቻለ ሲሆን በተቀሩት ስምንት ትምህርቶች ግን ለማስተዋል እንደተቻለው መምህራኑ ሙሉበሙሉ የበላይነትን ወስደው ራሳቸው የተለያዩ ተግባራትን ያከናውኑ ነበር፡፡ ይህም ጥንታዊ ወይም መምህር መራሽ የማስተማር ዘዴ የተከተለ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በተለይም ቋንቋን በማስተማር ረገድ ተማሪ መራሽ ዘዴን መከተል ውጤታማ እንደሚያደርግ ታምኖበት በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ ግን ምልከታ በተደረገባቸው አብዛኞቹ መምህራን ይህንን ዘመናዊ አቀራረብ ችላ በማት ትኩረታቸውን በጥንታዊ አቀራረብ ላይ እንዳደረጉት ተስተውሏል፡፡ ይህም ሁኔታ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ሃላፊነትን በመውሰድ የተለያዩ ተግባራትን የማከናወን ልምድ እንዲኖራቸው ሊያደረግ እንደማይችል መገመት አያዳግትም፡፡ ሌላው ደግሞ ጠያቂና መላሽን በተመለከተ የተደረጉ ምልከታዎች እንደሚያሳዩት በአብዛኞቹ ትምህርቶች የከፍተኛውን የጠያቂና የመላሽ ሚናን የሚይዙት መምህራኖች ናቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ተማሪዎች ሁል ጊዜ የተባሉትን ሁሉ ከመቀበል የዘለለ ያልገባቸውን የመጠየቅና ለሚጠይቋቸውም ጥያቄዎች ፈጥኖ መልስ የመስጠት ልምድን እንዳያካብቱ ተጽዕኖ ሊያሳድርባቸው ይችላል፡፡ አንብቦ መረዳትን በማስተማር ረገድ መምህራን ስላላቸው ሚና በጽሑፍ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሚከተለው መልኩ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡- አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ሂደት የመምህራኑ ሚና

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 22 | ምንባቡ በሚነበብበት ጊዜ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላት ፍች አብራራለሁ፡፡ | 3 | 2 | 1 | - |
| 25 | ምንባብ ተነቦ እንዳለቀ የምንባቡን ይዘት አብራራለሁ፡፡ | 5 | 1 | - | - |
| 21 | ምንባብ በሚነበብበት ጊዜ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንቀጾችን ይዘት አብራራለሁ፡፡ | 2 | 3 | 1 | - |
| 23 | ምንባቡ ተነቦ እንዳለቀ የምንባቡን ይዘት ተማሪዎች እዲያብራሩ አደርጋለሁ፡፡ | - | - | 2 | 4 |

መምህራን በጽሑፍ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጥዋቸው ምላሾች እንደሚያሳዩት፣ ሦስቱ መምህራን ሁልጊዜ፣ ሁለቱ አብዛኛውን ጊዜ፣ አንዱ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ በምንባብ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላትን ፍች እንደሚያብራሩ ከምላሻቸው ለመመልከት ተችሏል። የምንባቡን አጠቃላይ ይዘት ማብራራትን በተመለከተ አምስቱ መምህራን ሁል ጊዜ አንዱ ደግ አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ መልሰዋል። በምንባብ ውስጥ የሚገኙ አንቀጾችን ይዘት ሁለቱ ሁል ጊዜ፣ ሶስቱ አብዛኛውን ጊዜና አንዱ አንዳንድ ጊዜ እንደሚያብራሩ የመለሱ ሲሆን የምንባብን ይዘት ተማሪዎች እንዲያስረዱ ከማድረጉ አንፃር ደግሞ ሁለቱ መምህራን አንዳድ ጊዜ እንደሚተገበሩ ሲመልሱ አራቱ ደግሞ ፈጽሞ እንደማያደርጉ መልሰዋል። ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው፣ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ጊዜ አብዛኛዎቹ ተግባራት የሚከናወኑት በመምህራን ነው። ይህም አንድ ዘመናዊ አቀራረብን ተከትሎ ንባብን የሚያስተምር መምህር ሚና አንድን የሙዚቃ ኮንሰርት የሚመራ ባለሙያ ዓይነት ሚና ሊሆን ይገባል። በሌላ አባባል መረጃ የማቀበል ወይም አንድን ምንባብ የመግለጽ ሚና ሊኖረው አይገባም ከሚለው እሳቤ ጋር የሚቃረን ሲሆን፣ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ትምህርት ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዳይሆኑና ራሳቸው በራሳቸው ሃላፊነትን መሸከም የሚችሉ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል። ባጠቃላይ በሁለቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙት መረጃዎች ላይ በመመስረት መምህራኖቹ ተገቢ የሆነ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አሰጣጥን የተከተሉ አይደሉም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

## 4.3 የአንብቦ መረዳት ትምህርት ደረጃዎች

### 4.3.1 የቅድመ ንባብ ትምህርት

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎች አንድን ምንባብ ከሁነቶች ውጭ ያለ ዝግጅት እንዲያነቡ ማድረግ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህም የቋንቋ መምህራን ተማሪዎች አንድን ምንባብ የሚያነቡበትን ዓላማ እንዲያውቁ ማለትም ምክንያታዊ እንዲሆኑ በማድረግ ቅድመ ንባብን ሊያስተምሩ ይገባል። በዚህም መሠረት በሦስቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን ቅድመ ንባብን ምን ያህል እንደሚያስተምሩ ለመገንዘብ ምልከታዎች ተካሂደዋል። ከተካሄዱት አስራ ሁለት የንባብ ትምህርት ምልከታዎች በአራቱ ብቻ የቅድመ ንባብ ትምህርት የተከናወነ ሲሆን በተቀሩት ስምንት ትምህርቶች ግን ትምህርቱ ትኩረት እንዳልተሰጠው መገንዘብ ተችሏል። በተመሳሳይ ሁኔታም የቅድመ ንባብ

ትምህርት ትግበራን በተመለከተ መምህራን ላቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰንጠረዥ 2 ላይ ባሰፈረው መልኩ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡- የቅድመ ንባብ ትምህርት ትግበራ

| ተ.ቁ | መጠይቅ | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የቅድመ ንባብ ትምህርት እተገብራለሁ | 1 | 1 | 4 | |

በሰንጠረዥ ሁለት ላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው የቅድመ ንባብ ትምህርትን አንዱ ሁል ጊዜ እንደሚተገብር፣ አንዱ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ እንደሚያደርግና የተቀሩት አራቱ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚያስተምሩ ማስተዋል ይቻላል፡፡ በጥቅሉ በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት የተገኙት መረጃዎች ትንተና እንደሚያሳየን ለቅድመ ንባብ ትምህርት ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጠው መገንዘብ ይቻላል፡፡ በቅድመ ንባብ ትምህርት ወቅት የሚከናወኑ ተግባራት አይነትና እንዲሁም የተተግባሪነት ደረጃዎችን ለመቃኘት በተደረገው ጥረት በቅድመ ንባብ ትምህርት ጊዜ የቀረቡት ተግባራት አብዛኞቹ የምንባቡን ርዕስ ማብራራት ላይ ያተኮሩ ሲሆን አልፎ አልፎ ግን አዳዲስ ቃላት ፍቺን በመገመትና ቁልፍ ቃላትንም በማስተዋወቅ ላይ የተመሰረቱበት ሁኔታ እንዳለ ለማስተዋል ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የቅድመ ንባብ ትምርት ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ጉልህ ሚና ሊኖራቸው የሚችሉትን እንደ ትንበያ፣ ውይይት፣ ተማሪዎች ለምን እንደሚያነቡ ማሳወቅና ስዕሎች መጠቀምን የመሳሰሉት ተግባራት ትኩረት እንደተነፈጋቸው የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በመቀጠል መምህራን ቅድመ ንባብን ለማስተማር የሚጠቀሟ ቸውን ተግባራት በተመለከተ በጽሑፍ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጥዋቸው ምላሾች በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል

ሠንጠረዥ 5፡- የቅድመ ንባብ ትምህርት ተግባራት

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 13 | የቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ ውይይትን እጠቀማለሁ፡፡ | 1 | 1 | 3 | 1 |
| 14 | በቅድመ ንባብ ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ በመጠየቅ አስተምራሁ፡፡ | - | 1 | 4 | 1 |
| 15 | ተማሪዎች በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ቁልፍ ቃላትን ፍች እንዲገምቱ በማድረግ ቅድመ ንባብ ደረጃን አስተምራሁ፡፡ | 1 | 2 | 3 | |
| 16 | በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ የምንባቡን ርዕስ አብራራለሁ ፡፡ | 3 | 2 | 1 | |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ አብዛኛዎቹ መምህራን ቅድመ ንባብን ሲያስተምሩ የውይይት፣ የመተንበይና የቁልፍ ቃላት ፍቺ የመገመት ተግባራትን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፣ የምንባቡን ርዕስ ማብራራትን በተመለከተ ደግሞ አብዛኛዎቹ መምህራን ሁልጊዜ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ እናስተውላለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱ መምህራን ትንበያንና ውይይትን በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ ፈጽሞ ተግባራዊ እንደማያደርጉ የቀረበው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህም ሁኔታ በምልከታዎች ከተገኙት መረጃዎች ጋር ፍፁም ተመሳሳይ ነው ለማለት ባያስደፍርም ፣መሰረታዊ ልዩነት እንዳልተፈጠረ ግን ማጠቃለል ይቻላል፡፡ በዚህም መሠረት በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ ተማሪዎች ተነሳስኦትና ለማንበብ ውስጣዊ ዝግጁነት እንዲኖራቸው ለማድረግ መምህራኑ የሚያከናውኗቸው የተለያዩ ተግባራት ከብዛትና ከዓይነት አንፃር በቂ አይደሉም ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቅድመ ንባብ ትምህርትን በተመለከተ ተማሪዎች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መምህሩ የምንባቡን ርእስ በማስተዋወቅ በቀጥታ ወደ ማንበብ ተግባር ከመሸጋገር የዘለለ እንደ ውይይት፣ ትንበያም ሆኑ ሌሎች ተግባራትን ተጠቅመው የቅድመ ንባብ ትምህርትን እንደማያስተምሩ መልሰዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ከላይ የተሰጠውን ማጠቃለያ የበለጠ ያጠናክረዋል፡፡

### 4.3.2 የንባብ ጊዜ ትምህርት

የንባብ ጊዜ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ ራስ-መር በሆነ መልኩ ንቁ ተሳታፊ የሆኑ አንባቢ ተማሪዎችን መፍጠር ሲሆን ይህንን ከግብ ላይ ለማድረስ የሚያስችሉ ዝርዝር ዓላማዎችም ይኖሩታል፡፡ እነሱም፡- የምንባቡን አጠቃላይ ይዘት እንዲገነዘቡ፣ የምንባቡን መዋቅር እንዲተነትኑና የደራሲውን ዓላማ እንዲገነዘቡ ለመረዳት ነው፡፡ ስለሆነም የንባብ ጊዜ ትምህርት ቀዳሚው አላማ አንድን ጽሑፍ ማንበብ ሲሆን፣ ምንባቦችም በዝምታ ሊቀርቡ ይገባል (Harris and sipay 1990:102)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በክፍል ውስጥ የሚቀርበው የንባብ ትምህርት ለምን አላማ ምንና እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው የተገነዘቡ ውጤታማ ተማሪዎችን ለማፍራት የሚያግዝ በመሆኑ የትምህርቱ አቀራረብም ተማሪዎቹ በመምህሩ ወይም በተማሪዎቹ ከፍ ባለ ድምጽ የሚነበቡ ምንባቦች እንዲያዳምጡ ከማድረግ ተቆጥቦ አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቹ ራሳቸው በግልና በፀጥታ በሚያነቡበት መልኩ መሆን አለበት (Silbersten

1994,Nattall1992)፡፡ በዚህም መሰረት መምህራን አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ምንባቦችን እንዴት እንደሚያቀርቧቸው ለመለየት ምልከታዎች ተካሂደው የነበረ ሲሆን ምልከታ ከተካሄደባቸው አስራ ሁለት የምንባብ ትምህርቶች አስሩ ምንባቦች በተማሪዎች በጮክታ፣ ተራ በተራ፣ አንድ በአንድ የተነበቡ ሲሆን ሁለቱ ምንባቦች ደግሞ በመምህሩ ተነበዋል ። ተማሪዎች በግልና በዝምታ እንዲያነቡ የተደረገ ሙከራ ፈጽሞ አልነበረም፡፡ ተማሪዎች ተራ በተራ፣ በጮክታ በሚያነቡበት ወቅትም የተቀሩት ተማሪዎች መጽሐፍ ይዘው መከታተላቸዉንና አለመከታተላቸዉን ለመቆጣጠር በመምህራኑ በኩል የተደረገ አንዳችም ሙከራ አልተስተዋለም፡፡ እንዲሁም የተወሰኑ ተማሪዎች የሌላ ትምህርት መጽሐፍ ሲያገላብጡ ከመስተዋላቸውም በተጨማሪ ከሦስትና ከአራት የማያንሱ ተማሪዎች በመደገፊያቸው ላይ ተኝተው እንደነበር ለማስተዋል ተችሏል፡፡ ጥቂት ሲባሉ የሚችሉ ተማሪዎች ግን ለሁለትና ለሦስት አንድ መጽሐፍ ይዘው ይከታተሉ ነበር፡፡ ከዚህም በመነሳት ከምንባቡ አቀራረብና ከክፍል ቁጥጥሩ እንዲሁም ከተማሪዎች ባህሪይ አንፃር በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል ተገቢ የሆነ የምንባቦች አቀራረብ አልነበረም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

መምህራን አንብቦ መረዳትን ሲያስተምሩ ምንባቦች በማን እንደሚቀርቡ በጽሑፍ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጥዋቸው ምላሾች እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

ሠንጠረዥ 6፡- **የምንባቦች ትምህርት**

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 17 | አንብቦ መረዳትን ለማስተማር እያንዳንዱ ተማሪ በግልና በዝምታ እንዲያነብ አደርጋለሁ፡፡ | - | 1 | - | 5 |
| 18 | አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ተማሪዎችን ተራ በተራ እያስነሳሁ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ አደርጋለሁ | 3 | 2 | 1 | - |
| 19 | እኔ ራሴ በማንበብና ተማሪዎች እንዲያዳምጡን በማድረግ አስተምራለሁ፡፡ | - | - | 2 | 4 |

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኛዎቹ መምህራን አንብቦ መረዳትን የሚያስተምሩት ተማሪዎችን ተራ በተራ እያስነሱ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ

በማድረግ ነው። ከዚህም ሌላ ሶስቱ መምህራን አንዳንድ ጊዜ አንብቦ መረዳትን ራሳቸው በማንበብ እንደሚያስተምሩ ሲገልፁ የተቀሩት ግን ፈፅሞ ራሳቸው በማንበብ እንደማያስተምሩ መልሰዋል። ሌላው ደግሞ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር እያንዳንዱ ተማሪ በግልና በዝምታ እንዲያነብ በማደረግ የማስነበብ ዘዴን አምስቱ መምህራን ፈጽመው እንደማይጠቀሙበት ሲገልፁ አንዱ ግን አብዛኛውን ጊዜ እንደሚጠቀም መልሷል። ይህም ሁኔታ ከምልከታዎች ከተገኘው የምንባቦች አቀራረብ ባሕርይ ጋር የሚጣጣም ነው። ከዚህም በመነሳት ማጠቃለል እንደሚቻለው ምንም እንኳ ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማንበባቸው ንበታቸውን ለማሻሻል፣ አድማጭን ለመሳብ፣ ጥሩ አንባቢን ለማፍራትና አይናፋርነትን ለመቀነስ ጠቃሚ እንደሆነ ባይሰድም አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ግን ያለው ፋይዳ ከግልና ከዝምታ ንባብ ጋር የሚነጻፀር አይደለም፤ ማለትም አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ተገቢ የሆነው ዘዴ የግልና የዝምታ ንባብ ነው።ሆኖም ግን ለዚህ ተገቢ ለሆነው የንባብ ስልት ተገቢ የሆነ ትኩረት እንዳልተሰጠው የተገኙት መረጃዎች ያመለክታሉ።

### 4.3.3 የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

እንደሚታወቀው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መምህራን የሚያስርዋቸው ምንባቡ ተነቦ ካለቀ በኋላ ነው። ሆኖም ግን እንደ Zhenuyu (1997:42) አባባል መምህራ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ተማሪዎች ምንባቡን ምን ያህል እንደተረዱት ለማወቅ እንደሚያስችሏቸው ሁሉ የሚያነቡትን ምንባብ በተሻለ ደረጃ ለመረዳት እንደሚያስችሉም ተረድተው ሊጠቀሙባቸው ይገባል። የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የተማሪዎችን ቀደምት ዕውቀት በመቀስቀስ የማንበብ ፍላጎትን ሊጨምሩ ስለሚችሉ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጣቸው ለመመልከት የተሞከረ ሲሆን የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው መምህራኑ ምንባብ ከመነበቡ በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን እንደማይጠቀሙ ወይም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችንም እንዲያጤኗቸው ለማድረግ ምንም ዓይነት ሙከራ አለማድረጋቸውን ነው። ከዚህም ሌላ የምንባቦች አቀራረብ ሂደትን በተመለከተ መምህራን በጽሑፍ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፤

ሠንጠረዥ 7፡- የምንባብ ትምህርት አቀራረብ ሂደት

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 20 | ተማሪዎች ከማንበባቸው በፊት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲያጤኑ አደርጋለሁ | - | - | 2 | 4 |
| 24 | ምንባብ በሚነበብበት ጊዜ ወይም ተነቦ እንዳለቀ ምንባቡንመረዳትያለመረዳታቸውን እቆጣጠራለሁ፡፡ | - | 1 | 2 | 3 |

ከሠንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው ጥያቄ አንድን በተመለከተ ሁለቱ መምህራን አንዳንድ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ሲገልፁ፣ አራቱ ግን ፈጽሞ ተግባራዊ አድርገው እንደማያውቁ መልሰዋል፡፡ ጥያቄ ሁለትን በተመለከተ አንዱ መምህር አብዛኛውን ጊዜ፣ ሁለቱ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚተገበሩ የመለሱ ሲሆን የተቀሩት ሶስቱ ግን ፈጽሞ እንደማይተገብሩ መረጃው ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጥያቄ አንድና ሁለትን በተመለከተ ለተማሪዎችቃለመጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን ምላሻቸውምመምህራኑ ከላይ የተገለፁትን ተግባራት አከናውኗቸው እንደማያውቁ የሚያመለክት ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ ከዚህም በመነሳት ተማሪዎች አንድን ምንባብ አንብበው ለመረዳት ይችሉ ዘንድ የተደረገ ጥረት አልነበረም ለማለት ያስችላል፡፡ ባጭሩ ከላይ ከቀረበው መረጃ በመነሳት በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የምንባቦች አቀራረብ ዘመናዊነትን የተላበሰ አይደለም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

### 4.3.4 የድህረ ንባብ ትምህርት

የድህረ ንባብ ትምህርት አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ በውስጡ ያለው ይዘት የሚቃኝበትና የማጠናከርያ ስራም የሚሰራበት ነው፡፡ ይኸውም የተነበበውን ጽሑፍ ማጠቃለልና ምንባቡን ከተማሪዎች ዕውቀት፣ ዝንባሌና አመለካከት ጋር ማዛመድ ዓላማው ነው፡፡ በዚህም ወቅት የሚከናወኑ ተግባራት ከሚነበበው ጽሑፍ የሚወጡ ቢሆኑም በቀጥታ ምንባቡን የማይመለከቱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግንዛቤ ሊወስዱበት ይገባል (Williams, 1990:39) ፡፡

ይህም የንባብ ትምህርት ደረጃ ችላ ሊባል የሚገባው እንዳልሆነም ብዙ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ ከዚህም በመነሳት መምህራ የድኅረ ንባብ ትምህርት ደረጃን መተግበር አለመተግበራቸውን ለመለየት ምልከታዎች ተካሂደዋል፡፡

ምልከታ በተደረገባቸው አስራ ሁለት  የንባብ ትምህርቶች ሶስቱ ላይ ብቻ የድህረ ንባብ ትምህርት  የተሰጠ ሲሆን በተቀሩት  ዘጠኝ ትምህርቶች ግን እንዳልተተገበረ ለማስተዋል ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም  መምህራኑ  ድህረ ንባብ  ትምህርት ያስተምሩ እንደሆነ በጽሑፍ  ለቀረበላቸው ጥያቄ እንደሚከተለው  ምላሽ ሰጥተዋል፤

**ሠንጠረዥ 8 ፦ የድህረ ንባብ ትምህርት ትግበራ**

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 41 | የድህረ ንባብ ትምህርት አስተምራለሁ ፡፡ | 2 | 3 | 1 | |

ከላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የሚያመለክተው፣ ድኅረ ንባብን ሁለቱ መምህራን  ሁል ጊዜ፣ ሦስቱ  አብዛኛውን  ጊዜና  አንዱ ደግሞ አንድ አንድ ጊዜ እንደሚተገብሩ ነው፡፡ ይህም ሁኔታ በምልከታዎች ከተገኙት መረጃዎች ጋር የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም፡፡  ልዩነቱ ሊፈጠር የቻለው  በአጥኚው እምነት  መምህራኑ ስለድኅረ ንባብ ትምህርት ምንነት ጠቀሜታና ተግባራት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንንም ሀሳብ የበለጠ ለማጠናከር ለክፍል ደረጃዉ የተዘጋጀውን መማሪያ መጽሐፍ  ለመቃኘት የተሞከረ ሲሆን፣  በመጽሐፍቱ ውስጥም የድህረ ንባብ  ትምህርት  ክፍል አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለሆነም መምህራኑ ሌሎች  ክሂሎችን እንደ ጽሕፈት፣ ንግግርና ሥነ-ጽሑፍ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ክሂሎችን ለማዳበር ተብለው የቀረቡትን መልመጃዎችን ማስተማር  ድኅረ  ንባብን  እንደማስተማር  ስለሚወስዱ  ለቀረበላቸው  ጥያቄ  ከላይ የተመለከተውን  ምላሽ  ሰጥተዋል፡፡  በተመሳሳይ  ሁኔታ  የድኅረ  ንባብ  ትምህርትን በተመለከተ ለተማሪዎቹ የሚከተለው  ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፤

"ወደ ሌላ አዲስ ምንባብ ከመሸጋገራችሁ በፊት የተማራችሁትን ምንባብ በተመለከተ ካላችሁ እውቀትና ፍላጎት ጋር በማያያዝ የግል አመለካከታችሁን እንድታንፀባርቁ የሚያስችሉ እንደ ውይይት፣ ግምገማ፣ ክርክር፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ተግባራት ታከናውናላችሁ ሁ?" ተማሪዎች ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ የሰጡት ምላሽ እንደሚያ መለክተው አንድ ምንባብ ከተነበበ በኋላ ቀጥታ በስሩ የቀረቡትን መልመጃዎች ከማሠራት የዘለለ  ተማሪዎች  የተማሩትን  ምንባብ  ከቀደምት  ዕውቀታቸው፣  ፍላጎታቸውና አመለካከታቸው  ጋር  በማያያዝ እንዲገነዘቡ ለማድረግ በመምህራኑ በኩል የሚደረግ አንዳችም  ዓይነት  ጥረት  እንደሌለ  ነው፡፡  ስለዚህም  ከተማሪዎች  ቃለመጠይቅና

ከምልከታዎች የተገኘው መረጃ ሚዛን ይደፋል የሚለው የአጥኚው እምነት ነው። ከዚህም በመነሳት በትምህርት ቤቶች ተገቢ የሆነ የድኅረ ንባብ ትምህርት እየተሰጠ እንዳልሆነ ማጠቃለል ይቻላል ።

## 4.4 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### 4.4.1 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ባሕርይ

አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ሂደት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚካተቱት መልመጃዎችም ሆኑ በመምህሩ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ በባሕርያቸው የተማሪዎችን ተረድኦት ለመከታተል ብሎም ጥሩ አንባቢ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ የምንባቡን ይዘት ግልጽ ለማድረግ ወይም ለማደራጀትና ለማቀናጀት የሚረዱ መሆን አለባቸው። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው በምንባቦች ይዘትና ቅርጽ ላይ፣ የተለያዩ የአጠያየቅ ባሕሪን መሰረት ያደረገ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም በኑባሬያዊ ዐውድ የምናነብበት ዓላማ የተለያየ ስለሆነ ጥያቄዎችና ተግባራት በሚዘጋጁበት ጊዜ ይህንን እውነታ ከግምት ውስጥያስገቡ ሊሆን ይገባል። (Grellet, 1981:4)። በዚህም መሰረት የጥያቄዎቹ አጠያየቅ ባህሪን በተመለከተ የተደረገው ምልከታ እንደሚያሳየው ምልከታ ከተደረገባቸው አስራ ሁለት የአንብቦ መረዳት ትምህርቶች በሁለቱ ብቻ ተማሪዎች ምንባቡን እንዲያጠቃልሉ የተደረገ ሲሆን በተቀሩ ትምህርቶች የቀረቡት ግን አጫጭር ምላሽ የሚሹ እንደ እውነት-ውሸት፣ ቃላትን የማዛመድና የቃላት ፍችን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ናቸው። ከዚህም መረዳት የሚቻለው የተማሪዎችን ተረድኦት ለመገንዘብ የሚያስችሉ የተለያዩ የአጠያየቅ ባሕርያትን ያዘሉ መልመጃዎች ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ነው።

### 4.4.2 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ትኩረት ከዓይነት አንፃር

አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ሂደት መምህራኑ የሚያዘጋጇቸውም ሆኑ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚካተቱት መልመጃዎች የተማሪዎችን ስነ-ልሳናዊ ብቃት ብቻ ሳይሆን አእምሮታዊ እድገትንም ጭምር የሚያዳብሩ ሊሆኑ ይገባል። የሚቀርቡት ጥያቄዎችም በዓይነታቸው የተለያዩ የሆኑና የተለያየ የአጠያየቅ ባሕሪን መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው።

በዚህም መሠረት በተደረጉት ምልከታዎች ይቀርቡ የነበሩት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከትኩረትና ከዓይነት አንጻር ምን ይመስሉ እንደነበር ለመመልከት ተሞክሯል። ይኸውም ምልከታ በተደረገባቸው የአንብቦ መረዳት ትምህርቶች ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ወይም ሰፊ ሽፋን የነበራቸው ቀጥተኛ ጥያቄዎች ማለትም አጭር ምላሽ የሚሹ ሲሆን፣ ጥቂት የሚባሉ የትንበያ ጥያቄዎችም እንደነበሩ ለመመልከት ተችሏል። ከዚህም መረዳት የሚቻለው ሌሎች የጥያቄ ዓይነቶች እንደ አቋምን መግለጽና ግምገማን የመሳሰሉ ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ነው። በተመሳሳይ ሁኔታም ከተማሪዎች ጋር ቃለመጠይቆች የተደረጉ ሲሆን የተማሪዎች ምላሽም በምልከታዎች ከተገኘው መረጃ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል። ይኸውም ተማሪዎች አጭር ምላሽ ከሚሹ ጥያቄዎች በስተቀር ምንባቡን በተመለከተ ለምሳሌ የቋንቋ አጠቃቀምና ተገቢነትን ወዘተ. በመሳሰሉት ጉዳዮች ዙሪያ ግምገማ እንዲያደርጉ ብሎም የግል አስተያየታቸውን ወይም አቋማቸውን እንዲገልፁመ የሚጋብዙ ጥያቄዎች እንደማይቀርቡላቸው ከምላሻቸው ለመረዳት ተችሏል። ይህንንም ሁኔታ ለማረጋገጥ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ለመፈተሽ የተሞከረ ሲሆን፣ ውጤቱም በምልከታና በቃለመጠይቁ ከተገኘው መረጃ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ይኸውም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት አብዛኛዎቹ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ትኩረት ያደረጉት በእውነት - ውሸት፣ ቃላትን በማዛመድና የቃላት ፍችን በመጠየቅ ላይ ነው።

ከላይ ከቀረበው ትንተና መገንዘብ እንደሚቻለው ይቀርቡ የነበሩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀጥተኛ የጥያቄ ዓይነትን መሠረት ያደረጉ ማለትም አጫጭር ምላሽ የሚሹ፣ እንደ እውነት ውሸት፣ ማዛመድ፣ በግልጽ የተቀመጠ ሐሳብ የማስታወስና የቃላት ፍቺ፣ ወዘተ. የሚጠይቁ ናቸው። እነዚህም ጥያቄዎች ከክብደት አንጻር ሲታዩ ተማሪዎች ግልፅ የሆነን ሐሳብ እንዲያስታውሱ ወይም እንዲለዩ ከማድረግ በስተቀር የተደበቀን ሃሳብ ፈልገው እንዲያቀርቡ፣ የቀረበውን ሃሳብ እንዲገመግሙና ነገሮችን ከራሳቸው (ከህይወት ልምዳቸው ጋር በማገናኘት አስተያየት እንዲሰጡ የሚጋብዙ ዓይነት ጥያቄዎች አይደሉም። ባጭሩ ይቀርቡ የነበሩት ጥያቄዎች ምንም ዓይነት የውስብስብነት ባህሪይ አይታይባቸውም ማለት ይቻላል።

ከዚህም በመነሳት ጥያቄዎቹ ከአእምሮታዊ ክብደት አንፃር ሲታይ ተማሪዎች በቀጥታ የቀረበን ሐሳብ ከማስታወስ ያለፈ፣ የበለጠ አቅማቸውን ተጠቅመው የተለያዩ ተግባራትን እንዲያናውኑ የሚጋብዙ ዓይነት ስላልሆኑ የክብደት ደረጃቸው ዝቅተኛ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይቀርቡ የነበሩት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የተማሪዎችን አእምሮታዊ እድገት ከማዳበር አንፃር የሚኖራቸው ሚና ዝቅተኛ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ መምህራን አንብቦ መረዳትን ሲያስተምሩ ምንም አይነት ጥያቄዎችን እንደሚጠቀሙና ይበልጥ የትኛው ላይ እንደሚያተኩሩ በጽሑፍ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 9፡- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ትኩረት ከዓይነት አንጻር

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎች | - | 2 | 4 | - |
| 2 | ቀጥተኛ ጥያቄዎች | 5 | 1 | - | - |
| 3 | የትንበያ ጥያቄዎች | - | - | 5 | 1 |
| 4 | የግምገማ ጥያቄዎች | - | - | 3 | 3 |

ከላይ ከቀረበው መረጃ መመልከት እንደሚቻለው አራቱ አንዳንድ ጊዜ፣ ሁለቱ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎችን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ ቀጥተኛ ጥያቄዎችን በተመለከተ አምስቱ ሁል ጊዜ፣ አንዱ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚያስተምሩ ከምላሻቸው መረዳት የሚቻል ሲሆን፣ የትንበያና የግምገማ ጥያቄዎችን በተመለከተ ግን አብዛኞቹ መምህራን አንዳንድ ጊዜ የትንበያ ጥያቄዎችን እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ፣ አንዱ ግን ፈጽሞ እንደማይጠቀም መልሷል፡፡ በመጨረሻም የግምገማ ጥያቄዎችን በተመለከተ ሦስቱ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲስማሙ፣ ሶስቱ ግን ፈጽሞ ተጠቅመው እንደማያውቁ መልሰዋል፡፡ ይህም ሁኔታ በምልከታና በቃለመጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች ጋር ተመሳሳይነት ያለው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ፍፁም ተመሳሳይ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም አምስቱ መምህራን አንዳንድ ጊዜ የትንበያና አቋም የመግለጽ ጥያቄዎችን እንደሚጠቀሙ የገለፁ ሲሆን፣ ሶስቱ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የግምገማ ጥያቄዎችን እንደሚጠቀሙ መልሰዋል፡፡ ከዚህም መጠነኛ ልዩነቶች እንደተፈጠሩ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለልዩነቱም መፈጠር የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

ዓይነትን በተመለከተ መምህራኑ ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ መሆን ሲሆን እንደሚችል የአጥኚው ግምት ነው፡፡ ይኸውም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ ቀጥተኛ ምላሽ የሚሹ ናቸው፡፡ መምህራኑ ደግሞ ከመማሪያ መጽሐፍ ውጪ ሌሎች ስራዎችን እንደማይጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ማለትም የመጽሐፍ ጥገኞች ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ አጥኚው ከላይ ያስቀመጠውን ግምት ያጠናክረዋል፡፡ ስለሆነም ከምልከታና ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ሚዛን እንደሚደፉ የጥናቱ እምነት ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት ተማሪዎቹ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑና የግል ዕውቀታቸውንም ተጠቅመው ሐሳቦችን የመገምገም፣ በነገሮች አቋም የመያዝና የመግለጽ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ የሚበረታቱ፤ እንዲሁም ተረድኦታቸውንም ለመቆጣጠር የሚያስችሉየጥያቄ አይነቶች ትኩረት እንዳልተሰጣቸው ማጠቃለል ይቻላል፡፡

### 4.4.3 የአንብቦ መረዳት ስልቶች (Strategies) ትምህርት

የአንብቦ መረዳት ስልቶች ምንም እንኳ ተመሳሳይ ግብ ያላቸው ቢሆንም አጠቃቀማቸው ግን እንደምንባቡ ባህሪ፣ እንደ አንባቢው ዓላማና እንደ ንባብ ዐውዱ ሊለያይ ይችላል ፡፡ ጥሩ አንባቢም ይህን ስለሚገነዘብ ከሚያነብበት ምክንያት አንጻር የንባብ ስልቱን በማስማማት ያነባል(Nattall,1982)፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ጥሩ አንባቢ ይሆኑ ዘንድ መምህራን ስለንባብ ስልቶች ምንነትና አጠቃቀም ግልጽ የሆነ ትምህርት ሊሰጡ ይገባል፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ ምልከታዎች የተካሄዱ ሲሆን በምልከታዎቹም መምህራን ርእስ በማስተዋወቅ ወደ ማንበብ ተግባር ከመሂድና ምንባቡ ተነቦ ካለቀ በኋላ በቀጥታ መልመጃዎችን ከማሰራት ያለፈ ተማሪዎችን ከንባብ ስልቶች ጋር ለማስተዋወቅ ያደረጉት ምንም ዓይነት ሙከራ እንዳልነበር ለማስተዋል ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ተማሪዎች መምህራችሁ የተለያዩ የንባብ ስልቶች ለምሳሌ እንደማጠቃለል፣ መተንበይ፣ ዳግም ንባብ፣ ሐሳብን ማመንጨት፣ ቃላትን መገመት፣ ቃላትን መዝለል፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲኖራችሁና እንድትጠቀሙ የሚያደርጉት ጥረት ይኖር እንደሆነ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ የሰጡት ምላሽ በምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ከመገኘቱም በላይ አብዛኞቹ ተማሪዎች ለቃላቱ ባይተዋር እንደሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህራን የንባብ ስልቶች ትምህርትን በተመለከተ ለቀረቡላቸው የጽሑፍ መጠይቆች የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ10፡- የአንብቦ መረዳት ስልቶች ትምህርት

| ተ.ቁ | መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 46 | ተማሪዎች አንድን ምንባብ እንዴት ማጠቃለል እንዳለባቸው አስተምራለሁ፡፡ | | 1 | 1 | 4 |
| 48 | ተማሪዎች ሀሳብ ከማመንጨት ስልት ጋር እንዲተዋወቁ አደርጋለሁ፡፡ | | | | 6 |
| 49 | ተማሪዎች ቃላትን የመገመት ስልት እንዲገነዘቡ አደርጋለሁ፡፡ | | 1 | 4 | 1 |
| 47 | ተማሪዎች ከዳግመ ንባብ ስልት ጋር እንዲተዋወቁ አደርጋለሁ፡፡ | | 2 | 1 | 3 |
| 50 | ተማሪዎች ቃላትን የመዝለል ስልት እንዲገነዘቡ አደርጋለሁ፡፡ | 1 | | 5 | |
| 51 | ተማሪዎች እንዴት መተንበይ እንደሚችሉ አስተምራለሁ፡፡ | | 3 | 3 | |

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው የማጠቃለል ስልትን አራቱ መምህራን ፈጽመው አስተምረው የማያውቁ ሲሆኑ የተቀሩት ሁለቱ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜና አንዳንድ ጊዜ እንደሚያስተምሩ መልሰዋል፡፡ ተማሪዎችን ሐሳብ ከማመንጨት ስልት ጋር ማስተዋወቅን በተመለከተ ስድስቱም መምህራን ምንም ዐይነት ጥረት አድርገው እንደማያውቁ ማስተዋል ይቻላል፡፡ ቃላት መገመትን አንዱ አብዛኛውን ጊዜ፣ አራቱ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚያስተምሩ ሲገልጹ አንዱ ግን ፈፅሞ እንደማያስተምር መልሷል፡፡ የዳግመ ንባብ ስልትን ሁለቱ አብዛኛውን ጊዜ፣ አንዱ አንዳንድ ጊዜ እንደሚያስተምሩ ሲስማሙ ሦስቱ ግን አስተምረው እንደማያውቁ የመለሱ ሲሆን በመጨረሻም መተንበይን ሶስቱ አብዛኛውን ጊዜ፣ ሶስቱ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ መልሰዋል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው የመረጃዎች ትንተና ሐሳብ ከማመንጨት ስልት በስተቀር መምህራኑ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ሌሎች ስልቶችን እንደሚያስተምሩ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም በምልከታና በቃለመጠይቅ ከተገኙት መረጃዎችና ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች መካከል የተወሰነ ልዩነት እንደተፈጠረ ያመለክታል፡፡ ለልዩነቱ መፈጠርም የንባብ ስልቶች ምንነት፣ ጠቀሜታና አተገባበር በተመለከተ መምህራኑ ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ መሆን ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ይኸውም በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የንባብ ስልቶችን በተመለከተ በማስታወሻ መልኩ እንኳ የተቀመጠ ምንም ነገር ያለመኖሩና የመምህራኑ በመማርያ መጽሐፍቱ ላይ ጥገኛ መሆን ደግሞ ግምታችንን ያጠናክረዋል ፡፡ ይህንንም ከተደረገው ምልከታ በተጨማሪ መምህራኑ ከመማሪያ መጽሐፉ ዉጪ ሌሎች ይዘቶችን ራሳቸው

በማዘጋጀት አንብቦ መረዳትን ያስተምሩ እንደሆነ ለቀረበላቸው ክፍት ጥያቄ መጽሐፍ ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች ውጭ ሌሎች ይዘቶችን በራሳቸው አዘጋጅተው አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚያደርጉት ጥረት እንደሌለ ከምላሻቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለዚህም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ ቤተ-መጽሐፍት ውስጥ ቋንቋን በተመለከተ የተሰሩ የተለያዩ ስራዎችን ለማግኘት እድሉን አለማግኘታቸውን እንደምክንያት ለመጥቀስ ሞክረዋል፡፡ ስለሆነም በምልከታና በቃለመጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ሚዛን እንደሚደፉ የጥናቱ እምነት ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት አንብቦ መረዳትን ለማቀላጠፍ ከፍተኛ ሚና ያላቸውን የተለያዩ የንባብ ስልቶችን በማቅረብ ተማሪዎች እንዲያውቋቸውና ብሎም እንዲተገብሯቸው ከማድረጉ አንፃር በመምህራኑም ሆነ በመጽሐፉ አዘጋጆች በኩል የተደረገ ጥረት እንዳልነበረ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በቡልን ወረዳ በሚገኙ ሶስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች የ8ተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር መገምገም ነው። ለዚህም በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት፣ የመምህራንን የንባብ ደረጃዎች አተገባበር ሁኔታ፣ የንባብ ስልቶች ትምህረት፣ በንባብ ትምህርት አቀራረብ ሂደት ላይ ያላቸው ግንዛቤ፣ የንባብ በማስተማሩ ሂደት ያላቸው ሚና፣ በአንብቦ መረዳት ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በተመለከተ መረጃ ተሰብስቧል። የተሰበሰቡ መረጃዎችንም በተለያዩ ርዕሶች አደራጅቶ በመተንተን የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፤

1. የቅድመ ንባብ ትምህርት የተማሪዎችን ቀደምት ዕውቀት ለመለየት፣ የማንበብ ፍላጎታቸውን በማነሳሳት አጠቃላይ ምንባቡን ለመከታተል ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ እንዲሁም ተማሪዎች የሚያነቡበትን ዓላማ እንዲያውቁ ማለትም ምክንያታዊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል ደረጃ ነው። ስለሆነም ችላ ሊባል አይገባም። ይሁንና በተተኳሪ መምህራን ለዚህ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ደረጃ ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጠ የጥናቱ ውጤት አመልክቷል።
2. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የንባብ ጊዜ ትምህርት አቀራረብ ስንመለከት የተማሪችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር በሚያስችል መልኩ አልነበረም። ይኸውም በአብዛኛው ተማሪዎችን ከፍ ባለ ድምጽ ተራ በተራ( አንቀጽ በአንቀጽ) በማስነበብ ላይ የተመሰረተ ነበር። በአጠቃላይ ለግልና ለዝምታ ንባብ ትኩረት እንዳልተሰጠ መረጃዎች አመልክተዋል።
3. የድህረ ንባብ ትምህርት አላማ የተነበበውን ምንባብ ማጠቃለልና ከተማሪዎች እውቀት፣ ዝንባሌና አመለካከት ጋር ማዛመድ ነው። ይህንንም ደረጃ መምህራን ሚና ክንውን፣ ክርክር፣ ውይይት ማጠቃለል፣ ወዘተ. የመሳሰሉ ተግባራትን ተጠቅመው ማስተማር ይችላሉ። ይሁን እንጂ በሶስቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ መምህራን የድህረ ንባብ ትምህርትን ተገቢ መሆነ መልኩ እንደማይተገበሩ ተስተውሏል።

4. አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ሂደት ሰፊ ሽፋን የሚሰጣቸው፣ የተማሪዎችን ተረድኦት ለመከታተል ብሎም ጥሩ አንባቢ እንዲሆኑ ለማገዝና በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ ሀሳቦችን ግልጽ ለማድረግ እንዲረዱ ታስበው የሚዘጋጁት የአንብባ መረዳት ጥያቄዎች ናቸው። ሆኖም ግን ተተኳሪ መምህራን የሚጠቀሟቸው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በባህሪ፣ በዓይነትና በክብደት ደረጃ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና አእምሮአዊ እድገትን ከማዳበሩ አንጻር በጣም ውስንነት እንደሚታይባቸው የጥናቱ ውጤት አመልክቷል።
5. የንባብ ስልቶች አንብቦ መረዳትን ለማቀላጠፍ የሚኖራቸው ጠቀሜታ የጎላ እንደሆነ መገመት አያዳግትም። ስለዚህ መምህራን ስለ ንባብ ስልቶች ምንነትና አጠቃቀም ለተማሪዎቻቸው ግልጽ ትምህርት ሊሰጧቸው ይገባል። ይሁንና ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎች፣ የአንብቦ መረዳት የጀርባ አጥንት የሆኑትን የንባብ ስልቶች ባለቤት እንዲሆኑ ለማስቻል ያደረጉት ጥረት እንዳልነበረ ጥናቱ አመልክቷል።
6. አንብቦ መረዳትን ስናስተምር ዘመናዊ አቀራረብን እንከተል ካልን የመምህር ሚና አንድን የሙዚቃ ኮንሰርት የሚመራ አይነት ሊሆን ይገባል። በሌላ አገላለጽ መረጃ የማቀበል ወይም አንድን ምንባብ የመግለጽ ሚና ሊኖረው አይገባም። ከዚህም አንጻር የተተኳሪ መምህራን ሚና ስንመለከት የዋና ተዋናይ ሚና አይነት እንደነበር መረጃዎች አመልክተዋል።
7. አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ሂደት ዘመናዊ አቀራረብን ለመከተልም ሆነ ላለመከተል የመምህራኑ ግንዛቤ ተለውጦ ከፍተኛውን ቦታ ሊይዝ ይችላል። የዚህ ጥናት ተተኳሪ መምህራንም የአንብቦ መረዳት የትምህርት አቀራረብን በተመለከተ ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ እንደሆነ ለማስተዋል ተችሏል።

## 5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች

መምህራን አንብቦ መረዳትን በሚያስተምሩበት ወቅት የሚከተሏቸው የማስተማር ስልቶችና ብልሃቶች፣ በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። በዚህ ጥናት ውስጥም ተተኳሪ መምህራን አንብቦ መረዳትን በማስተማሩ ሂደት ጥንታዊ አቀራብን የተከተሉ መሆናቸውን ለመመልከት ተችሏል። ይህንን ችግር በመቅረፍ የተሻለ የአንብቦ መረዳት ትምህርት መስጠት ይቻል ዘንድ የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ተሰጥተዋል፤

- የንባብ ትምህርትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመስጠት ይቻል ዘንድ፣ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ወይም ኮሌጆች በመስኩ፣ ጥልቅ እውቀት ያካበቱ፣ ዘመናዊ አቀራረብን የተገነዘቡ፣ እንዲሁም አጠቃላይ ስለ አንብቦ መረዳት ትምህርት የላቀ ግንዛቤ ኖሯቸው የሚመረቁ መምህራን መኖር ግድ ይላል። ይሁን እንጂ ተተኳሪ መምህራን በኮሌጅ ቆይታቸው የንባብ ትምህርትን ተገቢ በሆነ መልኩ ለመተግበር የሚያስችል የተለየ ኮርስ እንዳልተሰጣቸው ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል። ይህም ሁኔታ ተተኳሪ መምህራን በአንብቦ መረዳት ትምህርት ላይ ያላቸው አጠቃላይ ግንዛቤ ዝቅተኛ ስለመሆኑና ጥንታዊ አቀራረብ ዘዴንም ስለ መከተላቸው እንደምክንያት ሊጠቀስ ይችላል። ስለዚህ ኮሌጆቹም ሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ለንባብ ትምህርት ትኩረት በመስጠት፣ ሰልጣኞች ስለ ንባብ ትምህርት የተለያዩ ምሁራን ከሚሰነዝሯቸው ዘመናዊ ጽንሰ ሃሳቦች ጋር እንዲተዋወቁ በማድረግ፤ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ቢፈጥሩ፤ ከላይ የተመለከተው ችግር ቀጣይነት ላይኖረው ይችላል።
- የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በተመለከተ መምህራኑ የታየባቸውን አነስተኛ ግንዛቤ በማሳደግ፣ዘመናዊ የማስተማር ዘዴን እንዲከተሉ የሚያስችሉ የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎችን በማዘጋጀት፣ መምህራኑ የሚሳተፉበትን ሁኔታ፤ ትምህርት ቤቶችም ሆኑ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ቢያመቻቹ ጠቀሜታ ይኖረዋል ።
- የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በተመለከተ የመምህራንን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎችን ከመስጠቱ ጎን ለጎን መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው መማሪያ መጽሐፍትም የሚሻሻሉበት ሁኔታ ቢፈጠር፤ ዘመናዊ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ለመስጠት አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ይኸውም ከመጽሐፍቱ ውስጥ ሶስቱም የአንብቦ መረዳት ደረጃዎች በቂና ተገቢ ከሆኑ ጥያቄዎች ጋር እንደገና ተሻሽለው የሚዋቀሩበትና አንብቦ መረዳትን ለማቀላጠፍ የሚያግዙ የተለያዩ የንባብ ስልቶች በማስታወሻ መልኩ እንደገና ተካትተው የሚቀርቡበት ሁኔታ ቢፈጠር የተሻለ ይሆናል ።
- በአንብቦ መረዳት ትምህርት ትግበራ ዙሪያ የመምህራኑ ግንዛቤ ዝቅተኛ እንዲሆንና ጥንታዊ አቀራረብን እንዲከተሉ ተፅእኖ ያደረጉባቸው የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉ ይታመናል። ይሁን እንጂ ግን መምህራን የንባብን ትምህርትን በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የተዘጋጁ የተለያዩ ስራዎችን በማንበብና ራሳቸውን ከዘመናዊ ትወራዎች ጋር

በማስተዋወቅ፣ ብቃታቸውን ለማዳበር ቢጥሩ፣ በአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር ላይ የተሻለ ግንዛቤ ሊያመጡ ይችላሉ።

- ✓ ውጤታማ የአንብቦ መረዳት ትምህርት ለመስጥ ሲታሰብ ፣ከመማሪያ መጽሐፉ፥ በተጨማሪ መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ አጋዥ መረጃ መሳርያዎች ወይም የንባብ ትምህርትን በተመለከተ የተዘጋጁ ሌሎች መጽሐፍት በትምህርት ቤቶች ከሚገኙ ቤተመጽሐፍት ውስጥ ሊኖሩ ይገባል። ስለሆነም የትምህርት ቤቶች ሀላፊዎች ሌሎች ከሚመለከታቸው አካላትጋር በመተባበር መጽሐፍቱ የሚሟሉበትን ሁኔታ በያመቻቹ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በሚያስተምሩበት ወቅት የተስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ከፍ ሲል የተሰነዘሩት የመፍትሔ ሐሳቦች ተግባራዊ ቢደረጉ የአንብቦ መረዳት ትምህርቱ የተሻለ ይሆናል።

# ዋቢ ጽሑፎች


ተክሉ እቋር (1996)፡፡ "ዘጠነኛ ክፍልን በሚያስተምሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች የንባብ ትምህርት አተገባበር፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡ (ያልታተመ)

አለም እሸቱ (1992)፡፡ *መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ፡፡* አዲስ አበባ ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

እንግዳ ዘውዱ (1992) ፡፡ "ቶፕ ዳውን (Top Down) የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡ (ያልታተመ)

የኔ ሰው ደሴ(1990)፡፡ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር ተራክቧዊ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት፡፡ (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቀ ሙሉ (1988)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡* አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

Best,J.W. (1981) *Research in Education*. New Delhi: Prentice Hall of India Private Limited.

Brownne, A. (1996), *Developing Language and Literacy 3-8*. London: Paul Chapman Publisher.

Byrne, Donn. (1983). *Teaching Oral English*" London: Longman.

Carter, R and Nunan, D. (1995). *Introducing Reading*: Pengun Books Ltd.

Chia,H.(2001). "Reading Activities for Effective Top-down processing" *English Teaching Forum*. Vol.39, N1, Pp 22-25

Dubin, F. and Bycina, D.(1991), "Academic Reading and the ESL/EFL Teacher" in Celce-Murcia, M.(ed.) *Teaching English as a Second or Foreign Language*.Boston Heinle and Heinle publisher.

Dudely Evans, T and St. John Maggie Jo (1998). *Development in English: For Specific Purpose*. Cambridge University Press.

Duke, N and Person, D.(1998). "Effective Practice for Developing Reading Practice" http://literacy.Unconn.Edu/com *Pre, htm.* Edinburgh: Nelson and Sons Ltd.Pp 81-10

. Gebhard.J.G(1999) *Teaching English as a Foreign or Second Language. Michigan:* The University of Michigans.

Gillian, Lazar(1993) *Literature and Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

Goodman, K. (1970). *Choosing Materials of Teaching Reading.* Detnonitt Wavne State University Press.

Goodman, K. (1986). "Basal Reader: A call for Action". *Language Art.*

Gough, P, Hover,W. and Peterson, C.(1996) "Some Observation on a Simple View of Reading" In Cornoldi C, and Oakhill, 1.(eds.) *Reading Comprehension Difficulties: Processes and Intervention.* New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates. Inco. PP. 1-13.

Grant, N. (1989) *Making the most of your Text Book.* London: Longman.

Greenwood, J.(1992) "Comprehension and Reading" in Abbot,G.and Wingard. P, (eds.), *The Teaching of English as an International Language: A practical Guide.* Edinburgh: Nelson and Sons, Ltd.

Grellet, F. (1981). *Developing Reading Skills.* Cambridge: Cambridge University Press.

Harmer, (1990),*The Practice of English Language Teaching,* London: Longman Group Ltd.

Harris, A. and Sipay, E.(1990), *How to Increase Reading Ability; a Guide to Developmental and Remedial Methods.* London: Longman Group Ltd.

Hyland,K.(1995), "Purpose and Strategy: Teaching Extensive Reading Skills." Kral,T.(ed).*English Teaching Forum.* Washington D.c Pp. 104-109.

Johanston, B.(1988).''Active Reading'' Modern English Teacher Journals. Boston: Heinle and Heinle Publisher. PP. 195-208.

Mason, G. (1981). *A Primer on Teaching Reading: Basic Concepts and Skills of the Early Elementary Years.* Illinois: Peacock Publishers.

May,F.B(1990), Reading as Communication: *A*n Interaction Approach.(3rd ed), New York: Macmillan Publishing Company.

Mei-yun, Y(1995) "Teaching Efficient EFL Reading" Inkral, Thomas (ed).*Teacher Development Making the Right Moves*. Washington, D.C. Pp.179-188.

Nunan, D.(1995), *Designing Tasks for the Communicative Classroom*. Cambridge: Cambridge University press.

Nunan, D. (1991), *Language Teaching Methodology*. Prentice P Hall.

Nuttal, Christine. (1982). "An experiment in reading comprehension at the college level."

Nuttall, C. (1988), *Teaching English*. New Delhi: Anmol Publications PVT.LTD.

Rosa Maria, Mera Rivas (1999) "Reading in Recent ELT Course Books". *ELT Journal*.

Nuttall, C. (1994) , *teaching Reading Skill in Foreign languages Heinemann Educational Books Ltd.*

Pahuja, N. P. (2002). *Teaching English*, Delhi: Anmol publications PVT. LTD.

Sadhu,A. N. and Amarjit S.(1980). *Research Methodology in Social: Sciences.* Bombay: Himalaya Pbulishing House

Sheng, H. J. (2000). "A Cognitive Model for Teaching Reading Comprehension" *The English Forum.*

Silber Stein, S. (1994). *Technique and Resources in Teaching Reading. Oxford.* Oxford university press.

Smith, F. (1985), *Reading.* Cambridge; Cambridge University Press.

Swaffor,J.;Arens,K and Byrnes,H.(1991)*Reading for Meaning* ;An Integrated Approach to Language Learning, New Jursey; prentice-Hall, Inc.

Tollefson, S(1996) "A system for improving Teachers' Questions." In Kral. Thomas(ed) *Teacher Development Making the Right Moves*. Washington D.C.

Ur, Penny(1996), *A Course in Language Teaching:* Practice and Theory Cambridge University.

Wallace, E (1993), Reading. Oxford: Oxford University Press.

Williams, R, (1986). "*Top Ten Principles for Teaching Reading*". English Language Teaching Journal.

Williams, E.(1984). *Reading in the Language classroom*. London: Mcmillan puplishes Ltd.

Weaver, C. (1976). *Grammar for Teachers*. Illinois: National council of Teachers of English.

Zhenyu, Z.(1997) "Intensive Reading ;Getting your Students to See the Forest as well as the Trees" *English Teaching Forum.*

አባሪ አንድ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሥነ-ትምህርት ኮሌጅ

የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

በቡለን ወረዳ በሚገኙ 1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች

የክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርት አቀራረብ መከታተያ ቅጽ

I. አጠቃላይ መረጃ

- ምልከታ
- የትምህርት ቤቱ ስም -----------------
- ቀን -------------------
- ምድብ-----------------------

1. መምህሩ ዕለታዊ ወይም ሳምንታዊ ዕቅድ ነበራቸው ☐ አልነበራቸውም ☐

2. የዕለቱ ትምህርት ርዕስ፡-______________________________________________

3. የዕለቱ ትምህርት ዓላማዎች፡-

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

II. የቅድመ ንባብ ትምህርት አተገባበር

1. የቅድመ ንባብ ትምህርት ነበር ☐ አልነበረም ☐

2. መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በቃል ☐ በሰሌዳ ላይ በመጻፍ
   አስተዋውቋል ☐ አላስተዋወቁም ☐

3. የምንባቡን ርእስ አብራርተዋል ☐ አላብራሩም ☐

4. በቅድመ ንባብ ጊዜ መምህሩ ለተማሪዎች የምንባቡን ርዕስ አስተዋውቀው ቀጥሎ
   ሊነሱ የሚችሉ ጉዳዮችን እንዲተነብዩ ያበረታታሉ ☐ አያበረታቱም ☐

5 . ከሚያነቡት ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚገናኝ ስዕል፣ ፎቶግራፍና ፖስተር በማሳየት
   ተማሪዎች እንዲወያዩ ያደርጋሉ ☐ አያደርጉም ☐

6. በምንባቡ ውስጥ ያሉ የአዳዲስ ቃላት ትርጉምን ተማሪዎች ቀድመው እንዲገምቱ
ያደርጋሉ ☐ አያደርጉም ☐

7. ተማሪዎች ለምን አላማ እንደሚያነቡ ያሳውቃሉ ☐ አያሳውቁም ☐

8. በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ቃላት ያሳውቃሉ ☐ አያሳውቁም ☐

9. በምንባብ ጊዜ ተማሪዎች ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መምህራን ቀድመው ይሰጣሉ ☐ አይሰጡም ☐

## III. የንባብ ጊዜ ተግባራት

1. መምህሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ከምንባቡ በፊት እንዲያጤኗቸው
አድርገዋል ☐ አላደረጉም ☐

2. ምንባቡ የቀረበው ተማሪዎች በግል ☐ በቡድን ☐ በዝምታ ☐ በጮክታ ☐
በማንበብ ነበር ።

3. ምንባቡ የቀረበው በመምህሩ ነበር ☐

4. ተማሪዎች በንባብ ጊዜ የሚያነቡትን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ ዋና ዋና ሃሳቦችን
በቅደም ተከተል ማስታወሻ እንዲይዙ አበረታትተዋል ☐ አላበረታቱም ☐

5. ተማሪዎች የሚያነቡትን ጉዳይ ከሕይወት ልምዳቸው ጋር እንዲያገናዝቡ
አበረታተዋል ☐ አላበረታቱም ☐

6. ተማሪዎች የተለያዩ የማንበብ ስልቶችን እንዲጠቀሙ አድርገዋል ☐
አላደረጉም ☐

7. መምህሩ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ምንባቡ እንዳለቀ ተማሪዎች እንዲሰሩ
አድርገዋል ☐ አላደረጉም ☐

## IV. የድህረ ንባብ ጊዜ ተግባራት

1. የድህረ ንባብ ትምህርት ነበረ ☐ አልነበረም ☐

2. መምህሩ ተማሪዎች ያነበቡትን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ የራሳቸውን አስተያየት
እንዲሰጡ አድርገዋል ☐ አላደረጉም ☐

3. መምህሩ ተማሪዎች ባነበቡት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ እንዲወያዩ አድርገዋል

አላደረጉም

4. መምህሩ ተማሪዎች ባነበቡት ርዕሰ ጉይ ላይ እንዲከራከሩ አድርገዋል

አላደረጉም

5. መምህሩ ተማሪዎች ባነበቡት ምንባብ ላይ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዴት ማውጣት እንዳለባቸው አለማምደዋል  አላለማምዱም

1. ተማሪዎች ካነበቡት ጽሑፍ ላይ አጠቃላይና ዝርዝር መረጃን እንዴት ማውጣት እንዳለባቸው አለማምደዋል  አላለማመዱም

2. መምህሩ ምንባቡን በተመለከተ ተማሪዎች ማጠቃለያ ሐሳብ እንዲሰጡ አድርገዋል  አላደረጉም

V. በንባብ ትምህርት አቀራረብ የመምህራን ሚና

1. የምንባቡን ይዘት በተመለከተ አጠቃላይ ገለጻ መስጠት
2. ጠያቂ
3. መላሽ
4. የትምህርቱን ሂደት መምራት
5. የክፍል አመራር
   - የሚሰጥዋቸው መመሪያዎች ግልጽ ነበሩ
   - የተማሪዎችን ስራ በመዟዟር ይቆጣጠራሉ
   - ተገቢ ሙገሳና ሂስ ይሰጣሉ
   - የተማሪዎች ተሳትፎ ከፍተኛ ነበር

VI. የንባብ ስልቶች ትምህርት

1. ተማሪዎች አንድን ምንባብ እንዴት ማጠቃለል እንደሚቻል ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ
2. ተማሪዎችን ሀሳብ ከማመንጨት ስልት ጋር ማስተዋወቅ
3. ተማሪዎች ቃላት የመገመት ስልትን እንዲገነዘቡ ማድረግ
4. ተማሪዎችን ከዳግም ንባብ ስልት ጋር ማስተዋወቅ
5. ተማሪዎች ቃላት የመዝለል ስልትን እንዲገነዘቡ ማድረግ
6. ተማሪዎችን ከትንበያ ስልት ጋር ማስተዋወቅ

VII. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የሚከተሉት አይነት ነበሩ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **ቀጥተኛ ጥያቄ** | | | | | |
| | 1.1 **የመለየት ጥያቄዎች** | | | | | |
| | • ንጽጽርን የመለየት ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ዝርዝሮችን የመለየት ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ምክንያትና ውጤት የመለየት ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ዋና ዋና ሃሳቦችን የመለየት ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ቅደም ተከተልን የመለየት ጥያቄዎች | | | | | |
| | 1.2 **የማስታወስ ጥያቄዎች** | | | | | |
| | • ዝርዝሮችን የማስታወስ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ምክንያትና ውጤት የማስታወስ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ንጽጽርን የማስታወስ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ዋና ዋና ሃሳቦችን የማስታወስ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ቅደም ተከተልን የማስታወስ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • የገጸባሕሪን ጠባይ የማስታወስ ጥያቄዎች | | | | | |
| 2 | **የትንበያ ጥያቄዎች** | | | | | |
| | • ዝርዝሮችን የመተንበይ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ምክንያትና ውጤት የመተንበይ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ንጽጽርን የመተንበይ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ዋና ዋና ሃሳቦችን የመተንበይ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ቅደም ተከተልን የመተንበይ ጥያቄዎች | | | | | |
| 3 | **የግምገማ ጥያቄዎች** | | | | | |
| | • አስተያየትን የመገምገም ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ጠቀሜታን የመገምገም ጥያቄዎች | | | | | |
| | • አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • ብቃትንና ተገቢነትን የመገምገምጥያቄዎች | | | | | |
| | • እውነታን ወይም ፈጠራን የመገምገም ጥያቄዎች | | | | | |
| 4 | **አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎች** | | | | | |
| | • የግል አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎች | | | | | |
| | • በተገቢነትና በቋንቋ አጠቃቀም ዙሪያ አስተያየት የመስጠት ጥያቄዎች | | | | | |

## አባሪ ሁለት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ

## ሥነ-ትምህርት ኮሌጅ

## የድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

በቡለን ወረዳ በሚገኙ 1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ለስምንተኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ መምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፡፡

ውድ መምህር፡-

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የስምንተኛ ክፍል የንባብ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ ከመምህራን መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ተገቢ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ የሙያው ባለቤቶች ትብብርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለሆነም እርስዎ ይህን መጠይቅ በትክክል በመሙላት የበኩልዎን ሙያዊ ድጋፍ እንዲያደርጉልኝ በትሕትና እጠይቃለሁ፡፡

ለሚያደርጉልኝ ትብብርም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

I አጠቃላይ መረጃ

1. የትምህርት ቤቱ ስም ______________________________
2. ፆታ____________________
3. የትምህርት ደረጃ ____________________________________
4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ዓቢይ ___________ ንዑስ _________
5. በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የሚያስተምሯቸው የተማሪዎች ብዛት ______________
6. ሳምንታዊ የክፍለ ጊዜ ብዛት __________________________
7. የተመረቁበት ዓመተ ምሕረት __________________________
8. በ1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት አማርኛን ያስተማሩበት የአገልግሎት ዘመን________________________
9. በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርሲቲ ለ1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል የንባብ ትምህርትን ለማስተማር የሚያስችል ኮርስ ወስደው ነበር አዎ ☐ አልወሰድኩም ☐
10. የ1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ተማሪዎችን አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚያግዝ ወርክ ሾፕ፣ ሴሚናር ወይም ስልጠና ተከታትለው ያውቃሉ ☐ አላውቅም ☐

II. ግንዛቤን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች

ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመልስነት ሊቀርቡ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ አምስት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ እነሱም 5 በጣም እስማማለሁ 4፣ እስማማለሁ 3. መወሰን ያስቸግረኛል 2. አልስማማም1. ጨርሶ አልስማማም የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በታች ክፍት ቦታዎች በሰንጠረዡ ላይ ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ በ "X" ምልክት ያመለክቱ፡፡

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የአንድን ምንባብ መልዕክት ለመረዳት ተማሪዎች የቁልፍ ቃላት ፍችን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ | | | | | |
| 2 | የአንድን ምንባብ መልዕክት ለመረዳት ተማሪዎች የእያንዳንዱን ቃል ፍች ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ | | | | | |
| 3 | ተማሪዎች ስለንባብ ደረጃዎች ምንነትና ባህሪያት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ቢደረግ በአንብቦ መረዳት ትምህርት ውጤታማ የመሆን ዕድላቸው ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል፡፡ | | | | | |
| 4 | ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት ከምንባቡ በተጨማሪ ካሏቸው የቀደምት እውቀት መረጃዎች ላይ መመስረት ይኖርባቸዋል፡፡ | | | | | |
| 5 | በንባብ ትምህርት ጊዜ አካባቢያዊ ጣልቃ ገቦች መኖራቸው የትምህርቱን ውጤታማነት ሊቀንስ ይችላል፡፡ | | | | | |
| 6 | ተማሪዎች በንባብ ጊዜ የሚያጋጥሟቸውን ከባድ ቃላት በማስታወሻ ደብተራቸው ሊመዘግቡ ይገባል፡፡ | | | | | |
| 7 | በ1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ምንባቦች በተማሪዎች ተራ በተራ በጮክታ (አንቀጽ በአንቀጽ) ሊነበቡ ይገባል፡፡ | | | | | |
| 8 | በ1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ምንባቦች በመምህራን መቅረብ አለባቸው፡፡ | | | | | |
| 9 | በ1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ምንባቦች በግልና በዝምታ መነበብ አለባቸው፡፡ | | | | | |

III. የክፍል ውስጥ ትግበራን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች

ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመልስነት ሊቀርቡ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ አምስት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ እነሱም 4፣ ሁልጊዜ 3. አብዛኛውን ጊዜ 2. አንዳንድ ጊዜ 1. ጨርሶ የሚሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በታች ክፍት ቦታዎች በሰንጠረዡ ላይ ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ በ "X" ምልክት ያመለክ

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የቅድመ ንባብ (pre-reading) ትምህርትን ተግባራዊ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 11 | በቅድመ ንባብ ትምህርት ጊዜ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ለመቀስቀስ የተለያዩ ተግባራትን አከናውናለሁ፡፡ | | | | |
| 12 | የቅድመ ንባብ ትምህርት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስላለ ብቻ አስተምራለሁ፡፡ | | | | |
| 13 | በቅድመ ንባብ ትምህርት ደረጃ ውይይትን እጠቀማለሁ፡፡ | | | | |
| 14 | በቅድመ ንባብ ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ እጠይቃለሁ፡፡ | | | | |
| 15 | ተማሪዎች በምንባብ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላትን ፍች እንዲገምቱ በማድረግ ቅድመ ንባብ ደረጃን አስተምራለሁ፡፡ | | | | |
| 16 | በቅድመ ንባብ ትምህርት ጊዜ የምንባቡን ርዕስ አብራራለሁ | | | | |
| 17 | አንብቦ መረዳን ሳስተምር እያንዳንዱ ተማሪ በግልና በዝምታ እንዲያነብ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 18 | አንብቦ መረዳን ሳስተምር ተማሪዎችን በየተራ በማስነሳት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 19 | አንብቦ መረዳን ሳስተምር ራሴ በማንበብ ተማሪዎች እንዲያዳምጡ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 20 | ተማሪዎች ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲያጤኑ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 21 | ምንባብ መሚነበብበት ጊዜ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አንቀጾችን አብራራለሁ፡፡ | | | | |
| 22 | ምንባብ መሚነበብበት ጊዜ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላት ፍች አብራራለሁ፡፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 23 | ምንባቡ ተነቦ እንዳለቀ የምንባቡን ይዘት ተማሪዎች እንዲያብራሩ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 24 | ምንባብ መሚነበብበት ጊዜ ወይም ተነቦ እንዳለቀ ተማሪዎች ምንባቡን መረዳት አለመረዳታቸውን እቆጣተራለሁ፡፡ | | | | |
| 25 | ምንባቡ ተነቦ እንዳለቀ የምንባቡን ይዘት አስረዳለሁ፡፡ | | | | |
| 26 | አንብቦ መረዳትን ለመለማመድ በንባብ ጊዜ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የመሚገኙ ጥያቄዎችን እጠቀማለሁ፡፡ | | | | |
| 27 | አንብቦ መረዳትን ለመለማመድ በንባብ ጊዜ እኔ ራሴ የማዘጋጃቸውን ጥያቄዎች እጠቀማለሁ፡፡ | | | | |
| 28 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች ዋና ሀሳቦችን የመለየት /የማስታወስ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራሉ፡፡ | | | | |
| 29 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች ምክንያትና ውጤት(የማስታወስ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራሉ ፡፡ | | | | |
| 30 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች የምንባቡን ዋና ሀሳብ መተንበይ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ | | | | |
| 31 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች ንጽጽርን በመለየት ላይ ያተኩራሉ፡ | | | | |
| 32 | የምጠይቃቸው ጥያቄዎች ምክንያትና ውጤትን በመተንበይ ላይ ያተኩራሉ፡፡ | | | | |
| 33 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች የገጸ ባህሪን ጠባይን በመለየት ላይ ያተኩራሉ፡፡ | | | | |
| 34 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች የገጸ ባህሪን ጠባይ መተንበይ ላይ ያተኩራሉ፡፡ | | | | |
| 35 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች ዝርዝር ሀሳቦችን መተንበይ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ | | | | |
| 36 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች እውነታን መገምገም ላይ ያተኩራሉ፡፡ | | | | |
| 37 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች የተማሪ አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል፡፡ | | | | |
| 38 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች የደራሲውን አስተያየት በመገምገም ላይ ያተኩራል ፡፡ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 39 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች በቋንቋ አጠቃቀም ላይ አስተያየት የመስጠት ጥያቄዎች ላይ ያተኩራሉ፡፡ | | | | |
| 40 | የምጠቀማቸው ጥያቄዎች ቃላትን በመጠየቅ ላይ ያተኩራሉ፡፡ | | | | |
| 41 | የድሕረ ንባብ (post- reading) ትምህርት አስተምራለሁ፡፡ | | | | |
| 42 | በድህረ ንባብ ትምህርት ደረጃ የማጠቃለል ተግባራትን እጠቀማለሁ፡፡ | | | | |
| 43 | በድህረ ንባብ ትምህርት ደረጃ ተማሪዎች እንዲከራከሩ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 44 | በድህረ ንባብ ትምህርት ደረጃ ተማሪዎች የሚና ክንውን (role playing) ተግባርን እንዲያከናውኑ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 45 | በድህረ ንባብ ትምህርት ደረጃ በቃላት ፍቺ ላይ አተኩራለሁ፡፡ | | | | |
| 46 | ተማሪዎች አንድን ምንባብ እንዴት ማጠቃለል እንዳለባቸው አስተምራለሁ፡፡ | | | | |
| 47 | ተማሪዎች ከዳግም ንባብ (Re-reading) ስልት ጋር እንዲተዋወቁ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 48 | ተማሪዎች ሀሳብን ከማመንጨት (Brain storming) ስልት ጋር አስተዋውቃቸዋለሁ፡፡ | | | | |
| 49 | ተማሪዎች ቃላትን የመገመት ስልት እንዲገነዘቡ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 50 | ተማሪዎች ቃላትን የመዝለል ስልት እንዲገነዘቡ አደርጋለሁ፡፡ | | | | |
| 51 | ተማሪዎች እንዴት መተንበይ እንደሚችሉ አስተምራለሁ፡፡ | | | | |

IV. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያልዎትን መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ፃፉ፡፡

52.የቅድመ ንባብ ትምህርት አስተምረው የማያውቁ ከሆነ ምክንያትዎ ምንድነው?

______________________________

______________________________

______________________________

______________

53.ወደ ሌላ አዲስ ክሂል ትምህርት ወይም ንባብ ከመሸጋገርዎ በፊት የድሕረ ንባብ ደረጃን የማይተገብሩ ከሆነ ምክንያትዎ ምንድነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

__________________________________________________

54. አንብቦ መረዳትን ለማለማመድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት የንባብ ስልቶች ጨርሰው ያላስተማሩ ከሆነ ምክንያትዎ ምንድነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

__________________________________________________

55.ንባብን ለማስተማር ሁልጊዜ የሚጠቀሟቸው ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ብቻ ከሆነ ምክንያትዎ ምንድነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

__________________________________________________

56.ንባብን ለማስተማር ደስተኛ ካልሆኑ ምክንያትዎ ምንድነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

__________________________________________________

# አባሪ ሦስት

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የስነ- ትምህርት ኮሌጅ

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

የአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ ከ8ኛ ክፍል ተማሪዎች መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

ዝርዝር ጥያቄዎች፡-

1. ማንበብ ከመጀመርህ/ሽ በፊት መምህርህ/ሽ ለምንና እንዴት? ማንበብ እንዳለብህ/ሽ በማሳወቅና እንዲሁም ፍላጎትህን/ሽን በመቀስቀስ አጠቃላይ ምንባቡን ለመከታተል (ለማንበብ) ዝግጁ እንድትሆን/ኚ፣ ለማበረታታት የሚያደርጉት የተለያዩ ጥረቶች አሉ? ካሉስ ምንድን ናቸው?
2. ምንባቦች፡ በማንና እንዴት ይነበባሉ?
3. ወደሌላ አዲስ ምንባብ ወይም ክሂል ከመሸጋገርህ/ሽ በፊት የተማርከውን/ሽውን ምንባብ በተመለከተ ካለህ/ሽ የቀደመ እውቀት ጋር በማያያዝ የግል አመለካከትህን/ሽን እንድታንፀባርቅ/ቂ የሚያስችሉ እንደ ውይይት፣ ግምገማ፣ ክርክር፣ ወዘተ. የመሳሰሉ ተግባራትን ታከናውናለህ/ኛለሽ?
4. በአንብቦ መረዳት ትምህርት ጊዜ መምህርህ/ሽ እንደ አቋምን መግለጽ፣ ቀጥተኛ፣ ግምገማ፣ ትንበያ፣ ወዘተ. የመሳሰሉ የጥያቄ አይነቶችን ይጠቀማሉ? ለየትኛውስ የጥያቄ አይነት ከፍተኛውን ትኩረት ይሰጣሉ?
5. መምህርህ/ሽ እንደ መተንበይ፣ ዳግመ ንባብ፣ ቃላትን መዝለል፣ ቃላትን መገመት፣ ማጠቃለል፣ ወዘተ. ከመሳሰሉት የንባብ ስልቶች ጋር እንድትተዋወቅ/ቂና ብሎም እንድትጠቀም/ሚ ጥረት ያደርጋሉ?
6. ማንበብ ከመጀመርህ/ሽ በፊት መምህርህ/ሽ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንድታጤን/ኚ ያደርጋሉ?
7. መምህርህ/ሽ ምንባብ እየተነበበ እያለ ወይም ከተነበበ በኋላ ተረድቶህን/ሽን ለመቆጣጠር የሚያደርጓቸው ጥረቶች አሉ? ካሉስ ምንድን ናቸው?

# አባሪ አራት

## የተጠኚ መምህራን ዳራ

| የትምህርት ቤቶች ስም | መምህር | የትምህርት ደረጃ | የትምህርት መስክ | | በኮሌጅ/በዩኒቨርሲቲ የወሰዱት ስልጠና | | ሥራ ላይ እያሉ የወሰዱት ስልጠና | | የማስተማር ልምድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዓቢይ | ንዑስ | ነበር | አልነበረም | ነበር | አልነበረም | |
| ቡለን 1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል | 1 | ዲፕሎማ | ቋንቋ | - | - | - | | - | 4 |
| | 2 | ዲፕሎማ | ቋንቋ | - | - | - | | - | 4 |
| ኤጋንቦና ኤቆንጤ1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል | 3 | ዲፕሎማ | ቋንቋ | - | - | - | | - | 2 |
| | 4 | ዲፕሎማ | ቋንቋ | - | - | - | | - | 4 |
| ባሩዳ 1ኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል | 5 | ዲፕሎማ | ቋንቋ | - | - | - | | - | 2 |
| | 6 | ዲፕሎማ | ቋንቋ | - | - | - | | - | 2 |

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለፀው የድህረ ምረቃ ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ መሆኑንና በጥናቱ የተጠቀምኩባቸው የመረጃ ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ደተያለ መርቆ

ፊርማ ______________

አድራሻ ______________

(ማስረከቢያ ቀን) 29-07-03